# የደብረ ገነት ቅዱስ አማኑኤል ወኪዳነ ምሕረት
# የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን
# መተዳደሪያ ደንብ






ጥር 29,2013/Feb.6,2021

14-16 South Morton Ave.
Morton, PA 19070

# መግቢያ

እኛ በሰሜን አሜሪካ በፔንሰልቫንያ ግዛትና በአካባቢው ኗሪ የሆንን ከውዲቷ ሀገራችን በተለያየ ምክንያት ብንወጣም ለኦርቶዶክስ ተዋህዶ እምነታችን ባለን ፅኑ ፍቅርና እምነት መነሻነት በፊላደልፊያ ከተማ በጥቂት የተዋህዶ ልጆች ጥረት በመሰባሰብ መካነ ፀሎት ስፍራችንን ለማደራጀት ባደረግነው ጥረት በአውሮፓያን አቆጣጠር ከ1996 ዓም ጀምሮ እስከ ሰኔ 1999 ዓም  በኪራይ ቤት የአምልኮ ተግባራችንን ስንከውን መቆየታችን ይታወቃል።

በልዑል እግዚሐብሔር ቸርነት ቁጥራችን እየተበራከተ በመምጣቱና የራሳችን የሆነ የቤተ ክርስቲያን ህንፃ ለመግዛት ያደረግነው ጥረት ሰምሮልን በደብረ ገነት ቅዱስ አማኑኤል ስም በሰኔ ወር እ.አ.አ.1999 ዓም በፊላደልፊያ ከተማ ህንፃ በመግዛት ይህንኑ አዲስ ቤተ ክርስቲያን በታላቅ ድምቀት መስከረም 19 ቀን 1999ዓም  በማስመረቅ ተገቢውን መንፈሳዊ አገልግሎት ለመቋደስ በቅተናል።

ይህ በእንዲህ እንዳለ በሀገር ቤት የተከሰተውን የፖለቲካ የጎራ ልዩነት መንስዔ ሆኖ ቅዱስ ሲኖዶሳችን በሁለት ጎራ የሀገር ቤትና የውጪ ሲኖዶስ በመባል በመከፈሉ የተነሳ በተለይ በውጭ ሀገር ያሉ አብያተ ክርስቲያናት ለሁለት በተከፈሉበት ወቅት ደብራችን ግን ከሁለቱም ጎራ በመራቅ እራሱን በገለልተኛነት ከ1996 ዓም እስከ 2018 ዓም ሲያስተዳድር የቆየና ያለንበት ሀገር ህግ በሚፈቅደው መሰረት የራሱን የመተዳደሪያ ደንብ በማውጣት በቁጥር 23-2860452  በ1954 በወጣው በአሜሪካን ፌዴራል መንግስት በግብር አዋጅ በሴክሽን 501(ሲ)(3) በተመለከተው ሕግ ተመዝግቦ ከግብር ነጻ ሆኖ ሥራውን ሲያከናውን ቆይቷል።

በድጋሚ የሀገር ቤቱን የፖለቲካ ወጀብ በመከተል በተከሰተው ድንገተኛ ለውጥ በሁለት ተከፍሎ የነበረው ቅዱስ ሲኖዶስ በአንድ በመጠቃለሉ የቦርድ አመራርም የቤተ ክርስቲያኒቱ አደረጃጀት በሚፈቅደው ቀኖና መነሻነት በቃለ አዋዲ ላይ በመመስረት በሰበካ ጉባኤ የሚተዳደር  መሆኑ በመታወጁ የቦርድ አመራርም ጊዜውን ጠብቆ መክሰም ሲገባው በአንዳንድ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያናት ግን  በፅንፈኛ ኃይሎች ግትር አቋም የቦርድ አስተዳደር ሰለባ ለመሆን በቁ። ከነዚህም አንዱ እኛ የመሰረትነው የደብረ ገነት ቅዱስ አማኑኤል ቤተ ክርስቲያን ነበር።

ይህ የቦርድ አመራር ከህግ አግባብ ውጭ ደብሩን ከሃያ አመታት ላላነሰ ጊዜ ከምስረታው ጀምሮ በጉልበታቸውና በክህነታቸው በማገልገል ላይ የነበሩትን መልአከ ገነት ዳኛቸው ታደሰ ደገፉን ከደብሩ ለማስወገድ ባደረገው ኢ. ፍታዊ ድርጊቱ በተቀሰቀሰ አለመግባባት ደብሩን ለአምስት ተከታታይ ሳምንታት በምእመናን ላይ ከመዝጋቱም በተጨማሪ የሀገረ ሰብከቱ ሊቀ ጳጳስ ሆነው በሲኖዶስ  የተሾሙትን ብፁዕ አቡነ ፊልጶስን እውቅና ከመንፈግ አልፎ ደብሩን ያገለግሉ የነበሩ ቄሲስ በላይ አፍኔንና መሪጌታ አባተ ገብሬን ከአገልግሎት በማግለሉ እኛ መስራቾቹም ምንም ሚና በሌላቸው የቦርድ አባላትና በጥቂት የሴራቸው ተባባሪ በሆኑ ደጋፊዎቻቸው የደረሰብንን መገፋት ፍትህ እስከምናገኝ በጊዚያዊነት የህንድ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያንን በመከራየት ከአንድ አመት ላላነሰ ጊዜ የሚከናወነው መንፈሳዊ አገልግሎት ከቀደመው ደብር የተገለሉትንና የሀገረ ስብከቱን ሊቀ ጳጳስ በመያዝ ለማስቀጠል ችለናል።

ይህ የእምነት አምባችን የሚመራው በቤተ ክርስቲያናችን የቀኖና ሥርዐት በመሆኑ የመተዳደሪያ ደንባችንም ቃለ አዋዲውን መነሻ በማድረግ የተዘጋጀና በ1954 በወጣው በአሜሪካን ፌዴራል መንግስት የግብር  አዋጅ በሴክሽን 501 (ሲ)(3) በቁጥ 83-3969443 ተመዝግቦ ከግብር ነጻ ሆኖ ሥራውን የሚያከናውን ይሆናል።ይህ መተዳደሪያ ደንብ ከላይ የተገለጠውን መሠረት በማድረግ የተዘጋጀ መሆኑን እየገለፅን ይህን የመጀመሪያ ረቂቅ የመተዳደሪያ ደንብ በእናንተ በምእመናን አስተያየት መዳበር እንዳለበት ስለምናምን በ 39 ገፆች በ29 አንቀፆች በቀረበው ረቂቅ ሰነድ ላይ ያላችሁን አስተያየትም ሆነ ጥያቄ በመሰንዘር ተገቢውን እርማት በጋራ ከውነን ሰናበቃ በጠቅላላ ጉባዔ በማፅደቅ ወደ አፈፃፀም የምናመራ መሆናችንን የመተዳደሪያ ደንብ አርቃቂ ኮሚቴው በታላቅ መንፈሳዊ አክብሮት ለእናንተ ለምእመናን ማቅረባችንን እንገልፃለን።

የቤተ ክርስቲያኑ መሥራቾች ከድሮው አማኑኤል ቤተ ክርስቲያን ተዘግቶብን ስንወጣ የቤተ ክርስቲያን ተቆርቋሪ ምዕመናን ተሰብስበን ብዙ ውይይትና ስብሰባዎች አድርገን በእግዚአብሔር ፈቃድ እና በአቡነ ፊልጶስ እርዳታ የቅዱስ አማኑኤል ወኪዳነ ምሕረት ቤተ ክርስቲያን ተመስርቶ በህንድ ኦርቶዶክስ  ቤተ ክርስቲያን በኪራይ በJanuary 6, 2019 በልደት በአል ዋዜማ የመጀምሪያው የቤተ መቅደስ አገልግሎት በመስራች አባላት /ኮሚቴ በሊቀ ጳጳስ አቡነ ፊልጶስ እና በዋና ካህን መልአከ ገነት ቄስ ዳኛቸው ደገፉ ቅዳሴ ቤቱ ተባርኮ አገልግሎት ተጀመረ ።የነዚህም መስራች አባላት ሥም ዝርዝር በዚህ መተዳደሪያ ደንብ በመጨረሻ ገጽ ላይ በዝርዝር ሰፍረዋል ።

የደረሰብን እንግልት ሳያሸንፈን ለሁለተኛ ጊዜ ምእመናን ገንዘባችንን ፣ ጉልበታችንን እና እውቀታችንን በማቀናጀት በአጭር ጊዜ ውስጥ ሁለንተናዊ ይዘቱን ያሟላ የቤተ ክርስቲያን ህንፃ በአምላክ ፈቃድና ቸርነት November 2019 ዓም ለመግዛት በቅተናል።

# በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ የደብረ ገነት ቅዱስ አማኑኤል ወኪዳነ ምሕረት ቤተ ክርስቲያን መተዳደሪያ ደንብ (Bylaw)

## አንቀጽ - 1
### የደብረ ገነት ቅዱስ አማኑኤል ወኪዳነ ምሕረት ቤተ ክርስቲያን

ሀ) በዚህ መተዳደሪያ ደንብ የተቋቋመዉ ቤተ ክርስቲያን ተጠሪነቱ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ሲኖዶስ ሥር ለተቋቋመው የፔንስልቬንያን ሀገረ ስብከት በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ የደብረ ገነት ቅዱስ አማኑኤል ወኪዳነ ምሕረት ቤተ ክርስቲያን በሚል ስያሜ የሚጠራ ይሆናል። ቤተ ክርስቲያኑ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ሕግና ደንብ መሠረት የተቋቋመ ሲሆን ፤ የፔንስልቬንያን ስቴት ሕግና ደንብ በማይፃረር ሁኔታ የተቋቋመ ሕጋዊ አካል ነው። ቤተ ክርስቲያኑ በፔንሰልቬንያ አትራፊ ያልሆኑ ድርጅቶች (non-profit organization) በሚቋቋሙበት ሕግና ደንብ መሰረት የተቋቋመ ሕጋዊ አካል ነዉ።

ለ) አድራሻ

ደ.ገ.ቅ. አማኑኤል ወኪዳነ ምሕረት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን
D. G. K. Amanuel and Kidane Mehret Ethiopian
Orthodox Tewahedo Church
14-16 S. Morton Ave, Morton, PA 19070

ሐ) የደብረ ገነት ቅዱስ አማኑኤል ወኪዳነ ምሕረት ቤተ ክርስቲያን ማህተም መስቀል ያለበት ክብ ቅርጽ ሆኖ በአማርኛና በእንግሊዝኛ ቋንቋ የተቀረጸ ይሆናል።

መ) የቤተክርስቲያኑ የሂሳብ ዓመት January 1 ቀን ጀምሮ December 31 ቀን የሚጠናቀቅ ይሆናል።

## አንቀጽ - 2
### ዓላማ

1) የደብረ ገነት ቅዱስ አማኑኤል ወኪዳነ ምሕረት ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን የተቋቋመው በጌታችን በመድኃኒታችንና በአምላካችን በኢየሱስ ክርስቶስ ትምህርት ላይ ተመሥርቶ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን ለዘመናት ተቀብላ ያቆየችውን ሥርዓተ እምነትና አምልኮት ለማካሄድና የጸሎት አገልግሎት ለመስጠት ነው።

2) በተመለከተው ሕግ በ1954 በወጣው በአሜሪካን ፌዴራል መንግስት በግብር አዋጅ በሴክሽን 501 (ሲ) (3) በቁጥር 83-3969443 ተመዝግቦ ከግብር ነጻ ሆኖ ሥራውን የሚያከናውን ይሆናል።

## አንቀጽ - 3

### ከኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን ጋር ስለሚኖረው ግንኙነት

1) እምነትን ፤ ሥርዐተ አምልኮትንና ተዋህዶ ሃይማኖትን በሚመለከት የደብረ ገነት ቅዱስ አማኑኤል ወኪዳነ ምሕረት ቤተ ክርስቲያን ከኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን የማይነጠል የቤተ ክርስቲያኑ ውህድ አካል ይሆናል።

2) ደብረ ገነት ቅዱስ አማኑኤል ወኪዳነ ምሕረት ቤተ ክርስቲያን የሚተዳደረው በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቅዱስ ሲኖዶስ ሥር ሆኖ በፔንስልቬንያ ሐገረ ስብከት ሥር ነው። በዚህ ደንብና አግባብ ባላቸው የፔንሰልቬንያ ስቴት ሕጎችና በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቃለ ዓዋዲ መሠረት በጠቅላላ ጉባኤ በተመረጡ የሰበካ መንፈሳዊ አስተዳደር ጉባኤ ይመራል።

## አንቀጽ - 4

### የቤተክርስቲያኑ ተግባርና ሥልጣን

ሀ) ቤተክርስቲያኑ የተቋቋመበትን ዓላማ ለማስፈጸም ከዚህ ቀጥሎ የተዘረዘሩትን ተግባራት ያከናውናል።

1. በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ሃይማኖት እምነት፥ ሥርዓትና ባህል መሠረት የአምልኮተ እግዚአብሔር አገልግሎት መስጠት።
2. በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ እምነትና ሥርዓት መሠረት የሥርዓት ቅዳሴ፥ የሥርዓተ ጥምቀት፤ የሥርዓተ ጋብቻ፤ የሥርዓተ ፍትሃትና የምክር አገልግሎት መስጠት።
3. የምዕመናንን ዕውቀት ማዳበር የሚያስችል የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ኃይማኖትን ታሪክ፤ ባህልና ቅዱሳት መጻህፍትን የሚመለከት ትምህርታዊ ፕሮግራም አዘጋጅቶ ማቅረብ።
4. የግእዝ፤ የዜማና የቅኔ ትምህርት የሚሰጥበት ፕሮግራምን ማዘጋጀት።
5. በአካባቢው ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ሃይማኖትን ለማጠናከር በሚደረገው ጥረት ከእህት ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያናት ጋር መተባበር።

ለ) የተቋቋመበትን ዓላማ ከግብ ለማድረስ የደብረ ገነት ቅዱስ አማኑኤል ወኪዳነ ምሕረት ቤተ ክርስቲያን ውል የመዋዋል፤ ዕርዳታና መዋጮ የመሰብሰብን ሥልጣን ጨምሮ አትራፊ ያልሆኑ ድርጅቶችን ለማቋቋም በወጣው አዋጅ እና በአሜሪካን ፌዴራል መንግስት በግብር አዋጅ በሴክሽን 501 (ሲ) (3) ላይ የተዘረዘረው አጠቃላይ ሥልጣን ይኖረዋል።

ሐ) የደብረ ገነት ቅዱስ አማኑኤል ወኪዳነ ምሕረት ቤተ ክርስቲያን ለትርፍ የተቋቋመ ድርጅት ባለመሆኑ ፖለቲካ ነክ በሆኑ ጉዳዮች ላይ እንዳይሳተፍ ይታገዳል።

## አንቀጽ - 5

### አባልነት

የቃሉ መንፈሳዊ አግባብ እንደተጠበቀ ሆኖ ለዚህ ደንብ አፈጻጸም በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ እምነትና መሠረት በጌታችን በመድኃኒታችን በኢየሱስ ክርስቶስ የሚያምኑና ዕድሜአቸው ከ18 ዓመት በላይ የሆኑ ሁሉ ከዚህ በታች የተጠቀሱትን በተጨማሪ የሚያሟሉ የደብረ ገነት ቅዱስ አማኑኤል ወኪዳነ ምሕረት ቤተ ክርስቲያን አባል ለመሆን ይችላሉ።

ሀ) አከታትለው ቤተ ክርስቲያን አንድ ዓመት የመጡ አባል መሆን ይችላሉ።

ለ) የቤተ ክርስቲያኑን ዓላማ ለማራመድ ለአገልግሎት ሲጠየቁ ፈቃደኛ ሆነው የሚቀርቡ።

ሐ) የቤተ ክርስቲያኑን ዕድገትና ልማት የሚያራምዱ።

መ) በአባላት ጠቅላላ ስብሰባ የተወሰነውን በቤተሰብ $30 ዶላር እና በግለሰብ $20 ዶላር መዋጮ በየወሩ ለመክፈል ፈቃደኛ የሆኑ።

ሠ) የቤተ ክርስቲያኑን መተዳደሪያ ደንብ ተቀብለው የሚያከብሩና በሥራ ላይ የሚያውሉ።

ረ) አባልነትን ለማረጋገጥ የሚሰጠውን የአባልነት መታወቂያ ትንሽ ደብተር በየወሩ በማቅረብ ወርሃዊ ክፍያ የሚያስመዘግቡ። ምርጫ በሚከናወንበት ጊዜ እንደ ድምፅ መስጫ ሆኖ ስለሚያገለግል በአግባቡ በመያዝ ሲጠየቁ የሚያቀርቡ።

## <u>አንቀጽ - 6</u>

### የአባልነት መብትና ግዴታ

1) መተዳደሪያ ደንቡን ተቀብሎ በተግባር ማዋል።

2) ለሰበካ መንፈሳዊ አስተዳደር ጉባኤ አባልነት ለመምረጥና ለመመረጥ።

3) ለደብረ ገነት ቅዱስ አማኑኤል ወኪዳነ ምሕረት ቤተ ክርስቲያን አባላት ጠቅላላ ጉባኤ ለውሳኔ በሚቀርቡ ጉዳዮች ላይ ሃሳብ የማቅረብ መብት አላቸው። ሆኖም የሰበካ መንፈሳዊ አስተዳደር ጉባኤ አባላትንና ሌሎች ኃላፊዎችን ለመምረጥ በሚደረግ ስብሰባ ድምጽ መስጠት የሚችሉት ምርጫው ከመካሄዱ በፊት ቢያንስ የአንድ አመት አባልነት መዋጮአቸውን በተከታታይ ያለማቋረጥ የከፈሉ ብቻ ናቸው።

4) የደብረ ገነት ቅዱስ አማኑኤል ወኪዳነ ምሕረት አባላት የሆኑ ሁሉ ቤተ ክርስቲያኒቱ የምትሰጣቸውን አገልግሎቶች በነፃ ያገኛሉ፤ ሆኖም አባላት ለሚያገኙት አገልግሎት በገዛ ፈቃዳቸው የተቻላቸውን ከመለገስ ይህ ደንብ አያግዳቸውም። የደብረ ገነት አማኑኤል ወኪዳነ ምሕረት ቤተ ክርስቲያን አባላት የሆኑ ሁሉ ምእመናን ያለክፍያ የሚያገኙት አገልግሎት:
የክርስትና (የጥምቀት) አገልግሎትና የዕለት ሞት (የሞተ ሰው) ፍትሐት ናቸው።

5) ማንኛውም የደብረ ገነት ቅዱስ አማኑኤል ወኪዳነ ምሕረት አባል ከቤተ ክርስቲያኑ አባላት አንድ ሶስተኛውን 1/3 (ሲሶ) ማስፈረም እስከቻለ ድረስ የአባላት አስቸኳይ ስብሰባ የማስጠራት መብት አለው።

## አንቀጽ - 7

### ከአባልነት መሰረዝና በድጋሚ አባል ስለመሆን

ሀ) አንድ አባል ከኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ሥርዓተ ትምህርት ፤ ሕግ ፤ ቀኖናና እምነት ተጻራሪ የሆነ ተግባር ፈጽሞ ሲገኝ እና ግብረ ገብነትን የሚቃረን ተግባር ሲያደርግ ከተገኘ በቤተ ክርስቲያኑ ካሕናትና በሰበካ መንፈሳዊ አስተዳደር ጉባኤው ተመክሮ ከድርጊቱ የማይመለስ ሲሆን፤

ለ) ከላይ እንደተጠቀሰው አባልነታቸውም ቢሰረዝም ቤተ ክርስቲያን መጥተው መጸለይና ማስቀደስ ይችላሉ፣ አባል ያልሆኑ ምእመናን በቤተ ክርስቲያኑ ውስጥ የመመረጥና የመምረጥ መብት አይኖራቸውም፣ የቤተ ክርስቲያን ስብሰባም በሚኖርበት ጊዜ ስብሰባው ላይ የመሳተፍ ወይንም የመሰብሰብ መብት የላቸውም።

ሐ) የአባልነት ክፍያቸውን ያለበቂ ምክንያት ከሶስት ወራት በላይ አቋርጠው ክፍያውን እንዲያሟሉ የጽሁፍ ማሳሰቢያ ደርሶአቸው ቀሪውን የአባልነት ክፍያ ሳያሟሉ ሲቀሩ ከአባልነት ይሠረዛሉ።

መ) አንድ አባል አባልነቱ የተሠረዘው ከላይ በአንቀስ 7 (ሀ) ከተዘረዘሩት ምክንያቶች በአንዱ ከሆነ አባሉ በራሱ ፈቃድ ጉዳዩን ለሰበካ ጉባኤው ሲያቀርብና አባሉ በካህናቶች ተመክሮና ተዘክሮ መስተካከሉ ከተረጋገጠ ሰበካ ጉባኤው ተመልሶ አባል መሆን እንደሚችል ካረጋገጠ ወደ አባልነቱ እንዲመለስ ይፈቀድለታል።

ሠ) አንድ አባል ከአባልነቱ የተሠረዘው ከላይ በአንቀስ 7 (ሐ) በተጠቀሰው ምክንያት ከሆነ አባልነቱ እስከ ተሠረዘበት ጊዜ ያላሟላውን ክፍያ እንዲያሟላ ተደርጎ ወደ አባልነት እንዲመለስ ይፈቀደለታል።

ረ) አንድ አባል ከአባልነት የሚሠረዘው የሚሰረዝበትን ምክንያት በቅድሚያ በጽሁፍ እንዲያውቀው ተደርጎ ውሳኔ ለሚሰጠው አካል የበኩሉን መከላከያ አቅርቦ ከታየለት በኋላ ይሆናል።

ሰ) አንድ አባል በዚህ ደንብ መሠረት የተወሰነውን የአባልነት ክፍያ ሲከፍል ቆይቶ ከአባልነት ቢሰረዝ እስከዚያ ጊዜ ድረስ የከፈለው ክፍያ ይመለስልኝ ብሎ የመጠየቅ መብት የለውም።

## አንቀጽ 8 - 1

### የሰበካ መንፈስዊ ጉባዔ ተግባር

የሰበካ መንፈሳዊ አስተዳደር ጉባኤ ተጠሪነቱ ለአባላት ጠቅላላ ጉባኤ ሆኖ ዓላማውን ለማስፈጸም የሚከተሉትን ተግባራት ያከናውናል፡-

1) የእግዚአብሔርን ወንጌል መንግሥት መስበክና ትምህርቱንም ማስፋፋት፣

2) የቤተ ክርስቲያንን መንፈሳዊ የአብነት እና ዘመናዊ ትምህርት ቤትን ማቋቋምና ማደራጀት፣

3) መንፈሳዊና ማኅበራዊ አገልግሎትን ለምእመናን ሁሉ ማዳረስ፣

4) የሰንበት ትምህርት ቤትን ማቋቋምና ማጠናከር፣

5) ለቤተ ክርስቲያን አገልግሎት የሚያስፈልጉትን ሁሉ ማሟላት፣

6) የቤተ ክርስቲያንን አስተዳደርና አገልግሎት በመንፈሳዊ ሕግና ሥነ ሥርዓት መምራት፣

7) ቤተ ክርስቲያንን በሀብትና በንብረት ራሷን ማስቻል፣

8) የቤተ ክርስቲያን ሀብትና ንብረት ቅዱስ ሲኖዶስ በሚያወጣው ሕግና ደንብ መሠረት እየተመዘገበ እንዲያዝ፣ እንዲጠበቅ፣ እንዲለማና እንዲያድግ ማድረግ፣የቤተ ክርስቲያናችን ንብረት የምእመናኑ ሲሆን የመሸጥም የመለውጥም መብት ያለው ምእመናኑ ነው፣ የቤተ ክርስቲያን የመሸጥ መለወጥ በአጠቃላይ ጉባኤ ይወሰናል።

9) ሕገ ቤተ ክርስቲያን በሚፈቅደው መሠረት ከሲኖዶስ የሚሰጡትን ሕግጋት ፣ ደንቦች፣ መመሪያዎች ፣ ትእዛዞችና ውሳኔዎችን መፈጸምና ማስፈጸም፣

10) በቅርብም ሆነ በሩቅ የሚገኙ ሰበካ መንፈሳውያን ጉባኤያት እርስ በርሳቸው ተባብረውና ተረዳድተው እንዲሠሩ ማድረግ፣

11) ልዩ ልዩ የምግባረ ሠናይ ድርግቶችን ማቋቋምና አገልግሎታቸውን ማሟላት፣

12) የሕንጻ እድሳትና ጥገና የመሳሰሉት ሥራዎች ሁሉ ወቅቱን ጠብቀው የሚፈጸሙበትን ዕቅድና መርሐ ግብር ማዘጋጀት፣ በተግባር መዋላቸውን መቈጣጠር፣

13) የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እምነት ተከታዮችን ብዛት፣ የሰበካውን ንብረት፣ ገንዘብ፣ ገቢና ወጪ የመሳሰሉትንም አኃዛዊ መረጃዎች / ስታቲስቲክስ/ በወቅቱ እየመዘገቡ ለየሚመለከታቸው አካላት በሪፖርት እንዲገለጽ ማድረግ፣

14) በዚህ መተዳደሪያ ደንብ መሠረት ማንኛውንም ቤተ ክርስቲያንን የሚመለከት ጉዳይ መፈጸምና ማስፈጸም፣

15) በዚህ አንቀጽ ከተራ ቁጥር 1 እስከ ቁጥር 14 የተዘረዘሩትን ተግባራት በቅድሚያ እያጠና ተገቢውን ማድረግና አስፈላጊም ሆኖ ሲገኝ ጉዳዩን ከሚመለከታቸው ግለሰቦችና ድርጅቶች ጋር እየተነጋገረ መፈጸምና ማስፈጸም።

16) የቤተ ክርስቲያኑን እድገት በማስመልከት የአጭርና የረዢም ጊዜ ፕላን በማውጣት ለአባላት ጠቅላላ ጉባኤ አቅርቦ ያጸድቃል ፤ በተግባር መዋሉንም ይከታተላል።

17) በቤተ ክርስቲያኑ ስም አስፈላጊ ውሎችን ይዋዋላል ፤ ክስ ይመሠርታል ሲከሰስም መልስ ይሰጣል። ሆኖም የሚገባው ውል ከ$5,000 (አምስት ሺህ ዶላር) በላይ የሚያስወጣ ከሆነ በቅድሚያ ለአባላት ጠቅላላ ጉባኤ አቅርቦ ያስፈቅዳል። አስቸኳይ የቤተ ክርስቲያን አባላትን ጠቅላላ ስብሰባ በመጥራት ዉልና ወጭዎችን በመመካከር ያስፈጽማል።

18) የሰበካ መንፈሳዊ አስተዳደር ጉባኤው በቤተ ክርስቲያኑ ስም ተመዝግቦ የሚገኘውን ሕንፃ መሸጥ ፤ መለወጥ ወይም በመያዣነት አስይዞ መበደር አይችልም። አስፈላጊ ሆኖ ካገኘው ግን ይህንን ጉዳይ በተመለከተ ብቻ የሚነጋገርና ውሳኔ የሚሰጥ ፤ ከ30 ቀን ያላነሰ ጊዜ በመስጠት አስቀድሞ ስለስብሰባው አጀንዳ ማስታወቂያ እንዲነገር በማድረግ በሚጠራ የአባላት ጠቅላላ ጉባኤ ላይ ጉዳዩን አቅርቦ ውይይት ከተደረገ በኋላ ከአባላት ¾ ኛው ከደገፉት በዚሁ ውሳኔ መሠረት ያስፈጽማል።

19) ለቤተ ክርስቲያኑ የሚሰጡ ስጦታዎችን ይቀበላል፤ በአግባቡ ተመዝግበው ገቢ እንዲደረጉ ያደርጋል።

20) እንደአስፈላጊነቱ የተለያዩ የሥራ ክፍሎችንና ንዑሳን ኮሚቴዎችን ያቋቁማል፤ መመሪያ ይሰጣል፤ የተቋቋሙበትን ዓላማ ተግባራዊ ማድረጋቸውን ይቆጣጠራል።

21) ሀ) የቤተ ክርስቲያኑ ሰበካ መንፈሳዊ አስተዳደር ጉባኤ (በሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴው) አቅራቢነት በዚህ መተዳደሪያ ደንብ በአንቀጽ 12 የተመለከቱትን የሥራ ክፍል ኀላፊዎችንና አባላትን ይመርጣል፡፡

ለ) ቋሚ አገልጋዮችን በተመለከተ የሰበካ ጉባኤው የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያኑን የገቢና የሥራ ሁኔታ እየተመለከተ እሠረ ክህነት ካላቸው መካከል በሃይማኖታቸው፣ በሥነ ምግባራቸው፣ በዕውቀታቸውና በሥራ ልምዳቸው እያወዳደረ በጉባኤ ወስኖ ምደባው እዲፀድቅለት የሐገረ ስብከቱን ጽሕፈት ቤት ይጠይቃል፡፡

ሐ) ገቢ ዐቅማቸው አነስተኛ በሆኑ አብያተ ክርስቲያናት ከካህናትና ከምእመናን በሚመረጡ አባላት ሥራው እንዲሠራ ያደርጋል፤

22) የሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤው የካህናትን ፤ ዲያቆናትና ልዩ ልዩ ሰራተኞች የሚተዳደሩበት የሥራ ደንብና መመሪያ ያወጣል። መመሪያው የአበል ክፍያን ፤ ፈቃድንና አንዳንድ አስፈላጊ የሆኑ ወጪዎች የሚከፈሉበትን ሁኔታ የሚያካትት ይሆናል።

23) ማንኛውም የሰበካ መንፈሳዊ አስተዳደር ጉባኤ አባል ለቤተ ክርስቲያኑ የሚሰጠው አገልግሎት በበጎ ፈቃድ ስለሆነ ለቤተ ክርስቲያኑ ከሚገኘው
ገቢ ተካፋይ አይሆንም። አንድ አባል በቤተ ክርስቲያኑ የሰበካ ጉባዔ ሥራ አስፈጻሚ ለቤተ ክርስቲያኑን አስፈላጊ የሆኑ እቃዎች በአንቀጽ ማዘዣ ከታዘዘ ተግባሩን ለማከናወን የተለየ ወጪ ካወጣና ለዚሁ ደረሰኝ ካቀረበ ያወጣው ገንዘብ ይመለስለታል ፤ ሆኖም ከካህናት ጉባኤ ተወክለው በሰበካ መንፈሳዊ ጉባዔ አባልነት ጉባኤው ውስጥ የሚያገለግሉት ካህናት በአስተዳደር ጉባኤ አባልነታቸው ሳይሆን በክህነት አገልግሎታቸው የሚያገኙትን አበል ወይም ድጎማ አይመለከትም።

## አንቀጽ 8 - 2

### የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ሰበካ መንፈሳዊ አስተዳደር ጉባኤ አባላት

የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ሰበካ መንፈሳዊ አስተዳደር ጉባኤ የአባላት ዓይነትና ብዛት፣ የአባላት አመራረጥ፣ የተመራጮች አባላት መመዘኛ ከዚህ በታች በተዘረዘሩት ድንጋጌዎች መሠረት ይፈጸማል፡፡

1. የአባላት ዓይነትና ብዛት

የአጥቢያው ቤተ ክርስቲያን መንፈሳዊ አስተዳደር ጉባኤ ከዚህ ቀጥሎ እንደተመለከተው ከቤተ ክርስቲያኑ አስተዳዳሪ ጋር ከአምስት ያላነሱ ከዘጠኝ ያልበለጡ አባላት ይኖሩታል፡፡ የቤተ ክርስቲያኑ አስተዳዳሪ ካህን ብቻ ቋሚ የሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤው አባል ይሆናሉ።

ሀ) የአጥቢያው ቤተ ክርስቲያን አስተዳዳሪ የጉባኤው ቋሚ ሰብሳቢ ይሆናል።

ለ) ከዚህ በታች በተራ በፊደል (ሐ) እና (መ) ከተጠቀሱት ምእመናን መካከል የአስተዳደር ችሎታ ያለው (ያላት) በዚህ ጉባዔ የሚመረጥ (የምትመረጥ) ምእመን የጉባኤው ም/ሰብሳቢ ይሆናል (ትሆናለች) ።

ሐ) ከአንድ የሰንበት ት/ቤት ወጣት ጋር ከሰበካው ምእመናን መካከል የሚመረጡ ሰባት ምእመናን የጉባኤው አባላት ይሆናሉ፤

መ) ከመደበኛ አገልጋዮች መካከል ለሰበካ ጉባዔ አባልነት የተመረጠው (የተመረጠችው) ምእመን የሰበካው ቤተ ክርስቲያን ጸሐፊ ይሆናል (ትሆናለች) ።

2. የአባላት አመራረጥ

ሀ) የካህናት ጉባኤ ተመራጮች እና ከካህናት መካከል የሚመረጡት አባላት መመዘኛ፥

1) ለአስተዳደር ሥራ ተገቢና ብቁ የሆኑ መደበኛ አገልጋይ ካህናት፣

2) ኢክርስቲያናዊ ሥነ ምግባር የማይታይባቸው፣ ኀጠኝነትና መሰል ተግባራት አስተሳሰባቸውን ያዛባዋል ተብለው የማይጠራጠሩ፣

3) ከትዕቢት፣ ከተንኮል፣ ከአድማ፣ ከስካር፣ ከፍቅረ ንዋይ የራቁ፣ ግብረ ገብነታቸው እና ትሕትናቸው የተመሰከረላቸው፣

4) ለቤተ ክርስቲያን አገልግሎት በጸሎት የሚተጉ፤ ለስብከተ ወንጌል የሚፋጠኑ ፤

5) የገንዘብ ጉድለት ያልተገኘባቸው፣ በሌላም ወንጀል ተከሰው በጉባኤ ያልተወሰነባቸው ወይም በፍርድ ቤት ያልተፈረደባቸውና በማናቸውም ሁኔታ መብታቸው በሕግ ያልተገደበባቸው ዕድሜያቸው ከ21 ዓመት በላይ የሆናቸው ይመረጣሉ፡፡

6) ከላይ የተዘረዘሩትን መመዘኛዎች ያፈረሰ ካሕን ማስጠንቀቂያ ተሰጥቶት የማይታረም ከሆነና አድራጎቱም በቤተ ክርስቲያኑ ውስጥ ምዕመናን የመከፋፈል አድራጎት መሆኑን የሰበካ ጉባዔው ከአረጋገጠ ከአባልነት እንዲገለል በጽሁፍ ሰበካ ጉባኤው ያሳውቃል። የምእመናን ጠቅላላ ጉባኤ ተጠርቶ በጉዳዩ ከተወያዩ በሗላ ጉባኤው የደረሰበትን ውሳኔ ለሐገረ ስብከቱ ሊቀ ጳጳስ ይልካል።

7) የቤተ ክርስቲያኑ አስተዳዳሪ የተሰጠውን አደራ በአግባቡ መወጣት  አቅቶት በቤተ ክርስቲያኑ ውስጥ የመከፋፈል ዝንባሌ ከታየ ምዕመናን 1/3 የቤ/ክ ቋሚ አባላት ፔትሽን አስፈርመው ለሰበካ ጉባኤ አቅርበው አጠቃላይ ጉባኤ እንዲጠራላቸው በደብዳቤ መጠየቅ ይችላሉ። ሰበካ ጉባኤው ፔትሽን የፈረሙትን አባልነት ካረጋገጠ በኋላ በቂ ጊዜ ሰጥቶ አጠቃላይ ጉባኤ ይጠራል። ከዚያ በኋላ ፔትሽኑ ላይ በተጠቀሰው ጉዳዩ ውይይት ተደርጎ በ 2/3 ድምፅ ከተደገፈ የሰበካ ጉባኤው ለሐገረ ስብከቱ ሊቀ ጳጳስ ሪፖርት አድርጎ ያስፈፅማል።

ለ) የምእመናን ጉባኤ ተመራጮች ከምእመናን ወገን የጾታ ልዩነት ሳይደረግ መመዘኛ፡-
1) በሕገ ቤተ ክርስቲያን የጸኑ፣ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ እምነት ተከታዮች በቤተ ክርስቲያኑ በአባልነት ተመዘግበው ቢያንስ ሁለት ዓመት ግዴታቸውን የተወጡ።
2) የአጥቢያ ነዋሪ (Delaware, New Jersey and Penn-sylva-niaበሌላም ስቴት ስለመሆናቸው ሕጋዊ የሆነ የነዋሪነት መታወቂያ ያላቸው፤
3) ኢክርስቲያናዊ ሥነ ምግባር የማይታይባቸው፣ ጎጠኝነትና መሰል ተግባራት አስተሳሰባቸውን ያዛባዋል ተብለው የማይጠረጠሩ፣
4) ከትዕቢት፣ ከተነኮል፣ ከአድማ፣ ከስካር፣ ከፍቅረ ንዋይ የራቁ፣ ግብረ ግብነታቸውና ትሕትናቸው የተመሰከረላቸው የገንዘብ ጉድለት ያልተገኘባቸው በሌላም ወንጀል ተከሰው በጉባኤ ያልተወሰነባቸው ወይም በፍርድ ቤት ያልተፈረደባቸውና በማናቸውም ሁኔታ መብታቸው በሕግ ያልተገደበባቸው፤
5) በአጥቢያው ነዋሪ የሆኑ ዕድሜአቸው ከ21 አመት በላይ የሆኑና ወይም አካላዊና ስነ ልቦናዊ ብቃት ታይቶ  ምእመናን ይመረጣሉ፡፡

ሐ) ከሰንበት ት/ቤት የሚመረጡ ቁጥራቸው ከምእመናን ወገን ሆኖ መመዘኛ
1) በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ሃይማኖት የጸኑ፣
2) በሰበካው ሰንበት ት/ቤት በአባልነት የተመዘገቡ፤
3) ዕድሜአቸው ከ21 አመት ጀምሮ  የሰንበት ተማሪ ስነ ልቦና ብቃት ታይቶ፤
4) ብቁ ችሎታ ያላቸውና በአስተዋይነታቸው የተመሰገኑ፤
5) በቤተ ክርስቲያኒቱ ዶግማ፣ ቀኖናና ሥርዓት የማይጠረጠሩ ወጣቶች የጾታ ልዩነት ሳይደረግ ይመረጣሉ፡

<u>አንቀጽ 9 - 1</u>

## የሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤ አባላት ምርጫ

ሀ) አስመራጭ ኮሚቴ

1. የቤተ ክርስቲያኑ ሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤ ጠቅላላ ስብሰባ (ምልአተ ጉባዔ) አምስት አባላት ያሉት አስመራጭ ኮሚቴ ያቋቁማል። የአስመራጭ ኮሚቴ ተመራጮች ከመካከላቸው ሊቀመንበርና ጸሐፊ ሆነው የሚያገለግሉ አባላትን ይመረጣሉ፡፡

2. የሰበካ መንፈሳዊ አስተዳደር ጉባኤ አባላት ምርጫ ከሚከናወንበት ዕለት 3 ወር (ዘጠና ቀናት) አስቀድሞ አስመራጭ ኮሚቴ ይቋቋማል።

3. የአገልግሎት ዘመናቸውን በሚፈጽሙ የሰበካ መንፈሳዊ አስተዳደር ጉባኤ አባላት ምትክ ምርጫ የሚከናወነው በታህሳስ ወር ወስጥ በመጨረሻው እሁድ /Last Sunday in December/ ይሆናል።

4. አስመራጭ ኮሚቴው ምዕመናን የሰበካ መንፈሳዊ አስተዳደር ጉባኤው አባል ሆነው ሊያገለግሉ ብቃት አላቸው ብለው የሚያምኑባቸውን አባላት የስም ጥቆማ ይጠይቃል። ኮሚቴው ጥቆማው ከአንድ ወር ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ እንደሚጠናቀቅ ለአባላት በቅድሚያ ያሳውቃል። በዚህ ጊዜ ውስጥ ኮሚቴው ጥቆማውን ማጠናቀቅ ካልቻለ የጊዜ ገደቡ እንዲራዘም ለአባላት ጠቅላላ ጉባኤ ጥያቄ በማቅረብ ያስፈቅዳል።

5. የጥቆማው ጊዜ ገደብ ካለፈ ከሁለት ሳምንት በኋላ አስመራጭ ኮሚቴው ተጠቋሚዎችን ለምዕመናን ያሳውቃል፤ በዚሁ ዕለት ምርጫው የሚከናወንበትን ቀን በይፋ ያሳውቃል። ምርጫው በሚከናወንበት ዕለት እጩዎች ራሳቸውን ለአባላት እንዲያስተዋውቁ ይደረጋል ወይም አስመራጭ ኮሚቴው ስለ ተጠቋሚዎቹ አጠር ያለ መግለጫ ይሰጣል።

6. አንድ ተጠቋሚ ለምርጫ ለመቅረብ ፈቃደኛነቱን ለአስመራጭ ኮሚቴው ካሳወቀ በኋላ በተለያየ ምክንያት የምርጫ ስብሰባ በሚደረግበት ዕለት ሳይገኝ ቢቀር አስመራጭ ኮሚቴው በሚሰጠው አጠር ያለ መግለጫ መነሻ አባላት በሚሰጡት ድምጽ አሸናፊ ከሆነ በዕለቱ አለመገኘቱ ከምርጫው አሸናፊነት አያግደውም።

7. በአባላት ጠቅላላ ስብሰባ ላይ ምርጫው ተካሂዶ ከፍተኛ ድምጽ ያገኙ እጩዎች የሰበካ መንፈሳዊ አስተዳደር ጉባኤው አባላት ሆነው እንዲሠሩ ይወሰናል። በእለቱ በተሰጠው ድምጽ ከተመራጭ እጩዎች በመቀጠል ከፍተኛ ድምጽ ያገኙት እጩዎች በተጠባባቂነት ተይዘው ይቆያሉ።

8. አስመራጭ ኮሚቴው ምርጫው በተጠናቀቀ በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ ዘመናቸውን ፈጽመው በሚለቁትና በተተኪዎች መካከል የሥራ ርክክብ መደረጉን ይከታተላል።

## ስለተተኪ አባላት

ለ) የማንኛውም የሰበካ መንፈሳዊ አስተዳደር ጉባኤ አባል የአገልግሎት ዘመን ሶስት ዓመት ይሆናል። ሆኖም አንድ የአስተዳደር ጉባኤ አባል የአገልግሎት ዘመኑን ከፈጸመ በኋላ ለሌላ ተጨማሪ የአገልግሎት ዘመን ሊመረጥ ይችላል። ከሁለት ተከታታይ የአገልግሎት ዘመን በኋላ ለመመረጥ ግን ቢያንስ ሶስት ዓመት መጠበቅ ይኖርበታል።

ሐ) አንድ አባል የምርጫ ጊዜው ከማብቃቱ በፊት በሞት ወይም በዝውውር ምክንያት በአንቀጽ 8-2 ተራ ቁጥር 2 ከ(ሀ) እስከ (ሐ) የተዘረዘሩትን የሚያሟላ መሆኑ ሲታወቅ ወይም በሌላ ምክንያት ቦታው ክፍት የሆነ እንደሆነ ባለፈው ምርጫ ከተመረጡት አባላት ቀጥሎ ከፍተኛ ድምጽ ያገኘው አባል ሆኖ ቦታውን ይተካል። በዚህ ዓይነት የሚተካ አባል ከታጣ እንደገና በካህናቱና ምዕመናኑ መንፈሳዊ ጉባዔ ድምፅ ብልጫ ተመርጦ የተባለውን ክፍት ቦታ በአባልነት እንዲተካ ይደረጋል። ተተኪውም አባል የሚያገለግለው የተተካው አባል ምርጫ ዘመን እስኪፈጸም ድረስ ይሆናል።

ከሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤ አባልነት ስለመልቀቅ
ማንኛውም የሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤ አባል አገልጎሎቱን ሊቀጥል የማይችልበት ምክንያት ካጋጠመው ሁኔታውን በጽሁፍ ለሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤው በማቅረብ ራሱን ከአገልግሎት ማግለል ይችላል።

መ) ከሰበካ መንፈሳዊ አስተዳደር ጉባኤ አባልነት ስለመወገድ ፤ አንድ የሰበካ መንፈሳዊ አስተዳደር ጉባኤ አባል በሚከተሉት ምክንያቶች ከአባልነት ሊገለል ይችላል፦
1. በዚህ መተዳደሪያ ደንብ በአንቀጽ 5 ላይ በተደነገገው መሠረት ከአንድ የደብረ ገነት ቅዱስ አማኑኤል ወኪዳነ ምሕረት ቤተክርስቲያን አባል የሚጠበቅ ግዴታውን አሟልቶ ካልተገኘ፤
2. የደብረ ገነት ቅዱስ አማኑኤል ወኪዳነ ምሕረት ቤተ ክርስቲያንን ሕልውና የሚጻረር ተግባር ፈጽሞ ከተገኘ ፤
3) ምዕመናን በፖለቲካ ፤ በዘርና በተለያዩ ምክንያቶች ለመከፋፈል የሞከረ፤ ወንጀል ፈጽሞ የተፈረደበት ሲሆንና የፈጸመው ወንጀል በቤተ ክርሲቲያኒቱ ሕልውና ላይ የሚንጸባረቅ ከሆነ፤
4) የሰበካ መንፈሳዊ አስተዳደር ጉባኤውን የሥራ እንቅስቃሴ የሚያደናቅፍ ተግባር በተደጋጋሚ ሆን ብሎ ከፈጸመ፤
5) የቤተክርስቲያኑን ንብረትና ገንዘብ ያለአግባብ ያባከነና እንዲባክን ተባባሪ የሆነ፤ ከሰበካ መንፈሳዊ አስተዳደር ጉባኤ አባልነቱ ይወገዳል።

ሠ) አንድ የአስተዳደር ጉባኤ አባል ከኃላፊነቱ ከመወገዱ በፊት የፈጸመው ጥፋት በጽሁፍ ተገልጦለት የበኩሉን ማስረጃ በማቅረብ የመከላከል መብት ይኖረዋል።

## አንቀጽ 9 - 2

ስለሚሾሙ ፤ ስለሚቀጠሩና በበጎ ፈቃድ ቤተ ክርስቲይን ስለሚያገለግሉ

1.የደብር አስተዳዳሪ መመዘኛ
እንድ ካህን የደብር አስተዳደር ሆኖ ለመሾም የሚከተሉትን መመዘኛዎች ማሟላት አለበት፡

ሀ) ክህነት ያለው እና እድሜው ከ30 ዓመት በላይ የሆነ

ለ) ቀድሶ ማስተማር የሚችል ቢቻል የሐዲሳት፡ የብሉያትና የሊቃውንት መጻሕፍት የትሩጓሜ ትምህርት ከሶስቱ አንዱን የተማረ ወይም ከመንፈሳዊ ኮሌጅ በዲፕሎማ ወይም ከዚህ በላይ የተመረቀ

ሐ) በአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ቅን አገልግሎት የሰጠ

መ) በሥነ ምግባሩ እና በአርኣያ ክህነቱ የተመሰከረለት

ሠ) የአስተዳደር ልምድ ያለው ሰበካ ጉባዔው ከቤተ ክርስቲያኑ ካሕናት ጉባዔ አባላት ውስጥ ለቤተ ክርስቲያኑ አስተዳዳሪ ለመሆን ከላይ የተጠቀሱትን መመዘኛ የሚያሟላ የመንፈሳዊ ካሕን መርጦ ለምእመናኑ አቅርቦ በድምፅ ብልጫ ከተወሰነ በሗላ ለሐገረ ስብከቱ ሊቀ ጳጳስ እንዲሾሙለት በደብዳቤ ይጠይቃል።

2) ስለሚቀጠሩ ካህናትና ዲያቆናት

ሀ) ካህን (ቄስ)

1. መዝገብ ቅዳሴ የተማረ፣ሰዓታት፣ኪዳን፣ ሊጦንና መስተብቁዕ አጠናቆ ያወቀ ሰባቱን ምሥጢራት ቤተ ክርስቲያን ያጠና ግብረ ገብነቱ የተመሰከረለት።
2. ለምእመናኑ በተግባርም ሆነ በትሕትናው ምሳሌ የሚሆን
3. አብሮ መስራት የሚችል ፤ የቤተ ክርስቲያኑን ዓላማ ተቀብሎ የሚያራምድ
4. ከሰበካ ጉባዔውና ከቤተ ክርስቲያኑ አስተዳዳሪ የሚሰጡትን መመሪያዎች ተቀብሎ በስራ ላይ የሚያውል
5. ምዕመናን ያለምንም ልዩነት የሚያስተናግድና የሚያገለግል

ለ) ዲያቆን

የቃል ትምህርት ያጠና ፤ ዳዊት የደገመና አምስቱን አዕማደ ምሥጢር ያወቀ ግብረ ዲቁናና ሰዓታት የተማረ፤ግብረ ገብነቱ የተመሰከረለት።

ሐ) ሰባኬ ወንጌል

ቢቻል ከመንፈሳዊ ኮሌጅ በዲፕሎማ ወይም በድግሪ የተመረቀ ከአብነት ትምህርት ቤት የሐዲስ (የብሉይ) ትርጓሜ የተማረ።

መ) መሪጌታ

ጸዋትወ ዜማ ፣ አቋቋምና ቅኔ የሚያውቅ።

3) በበጎ ፈቃድ የሚያገለግሉ ካህናት ፣ዲያቆናት ፣ሰባክያነ ወንጌልና መሪጌቶች ክህነታቸው በትክክል የታወቀ ግብረ ገብነታቸው የተመሰከረላቸው እየተጣራ እንደየችሎታው እየተመደቡ ያገለግላሉ።

# አንቀጽ - 10

## የሰበካ መንፈሳዊ ጉባዔ ስብሰባዎች

1.የስብሰባ ቦታ

የሰበካ መንፈሳዊ አስተዳደር ጉባኤው ስብሰባዎች በሞርተን ከተማ ይደረጋሉ። አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝና የቴክኖሎጂው አቅም ሲፈቅድ አባላት በአካል ካልተገኙ በስልክ ወይም በዙም የስብሰባው ተካፋይ መሆን ይችላሉ።

2.መደበኛና አስቸኳይ ስብሰባ

የሰበካ መንፈሳዊ አስተዳደር ጉባኤው በየወሩ መደበኛ ስብሰባ ያደረጋል። አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘ የሰበካ መንፈሳዊ አስተዳደር ጉባኤው ሰብሳቢ ወይም ከጉባኤው አባላት አምስቱ ከጠየቁ አስቸኳይ ስብሰባ ሊጠራ ይችላል። ስብሰባውን የሚመራው የሰበካ መንፈሳዊ አስተዳደር ጉባኤው ሰብሳቢ ይሆናል። የስብሰባው አስፈላጊነት በቅድሚያ ለአባላት መገለጥ ይኖርበታል።

3.ምልዐተ ጉባኤ

የፔንስልቫኒያን ሕግ የማይቃረን እስከ ሆነ ድረስ አባላት 50% + 1 (ከግማሽ በላይ) ከተገኙ ምልዐተ ጉባኤ ሆኖ ስብሰባ ይጀመራል።

4.ቃለ ጉባኤ

ሰበካ መንፈሳዊ አስተዳደር ጉባኤው ፀሐፊ የአስተዳደር ጉባኤ ስብሰባዎችን ቃለ ጉባኤ በጽሑፍና በሪኮርድ አዘጋጅቶ ያቀርባል። የተዘጋጀው ቃለ ጉባኤ በሚቀጥለው ስብሰባ ላይ በንባብ ይሰማል፤ በቃለ ጉባኤው ላይ ለውጥ መደረግ ካለበት ይኸው ለውጥ በዕለቱ ስብሰባ ቃለ ጉባኤ ላይ እንዲካተት ይደረጋል። ሁሉም ቃለ ጉባኤዎች በሰብሳቢውና በጸሐፊው ይፈረማሉ። ሁሉም የሰበካ ጉባዔ ይፈርምበታል።

5.በድምጽ ብልጫ ውሳኔዎችን ስለማሳለፍ ማንኛውም የሰበካ መንፈሳዊ አስተዳደር ጉባኤው ውሳኔ በድምጽ ብልጫ ይወሰናል በአብዛኛው ድምጽ የተላለፈ ውሳኔ ተፈጻሚ ይሆናል።

## አንቀጽ - 11

### የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ሰበካ መንፈሳዊ አስተዳደር ጉባኤ
### (ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ) ሥልጣንና ተግባር

በዚህ መተዳደሪያ ደንብ አንቀጽ 2 እና 4 የተዘረዘሩትን ዐላማና ተግባር እየፈጸመ በተጨማሪ የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ሰበካ መንፈሳዊ አስተዳደር ጉባኤ (ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ) የሚከተለው ሥልጣንና ተግባር ይኖረዋል፡፡

1. የቤተ ክርስቲያን ሕግ በሚፈቅደው መሠረት የቤተ ክርስቲያንን እምነት፣ ሥርዓት እና ሲኖዶሳዊ መዋቅር የመጠበቅና የማስጠብቅ ግዴታ ይኖርበታል፡፡

2. ስለ ንዋይ ቅድሳት፣ ስለ ቅዱሳት መጻሕፍት፣ ስለ ልዩ ልዩ ታሪካዊ ቅርሶች አጠባበቅ፣ አያያዝ አያጠና ይመክራል፣ ይጠብቃል፤ ያስጠብቃል፡፡

3. በአጥቢያ ሰበካ ውስጥ የሚነሱትን የሃይማኖትና የምሥጢራተ ቤተ ክርስቲያን ጉዳይ የሚመለከት ልዩ የካህናት ጉባኤ ያቋቁማል፡፡

4. በሥርዓት ቤተ ክርስቲያን ጋብቻቸውን በፈጸሙ ባልና ሚስት መካከል የሚቀርቡትን ክሶች እና እንዲሁም ሥልጣነ ክህነትን እና ልዩ ልዩ ምሥጢራተ ቤተ ክርስቲያንን የሚመለከቱ ጉዳዮች ሁሉ ሰበካ ጉባኤ በሚሰይመው የካህናት ጉባኤ እንዲወሰን ያደርጋል፡፡ ጉዳዩ ከዚህ ጉባኤ ሥልጣን በላይ ሆኖ ከተገኘ ደረጃውን ጠብቆ ወደ በላይ አካል ያቀርባል፡፡

5. የሰንበት ት/ቤት ወጣቶችን ከክፉ ነገር ሁሉ የመጠበቅ፣ የሚሰጣቸው ትምህርትም ሆነ የሚዘምሩት መዝሙር በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ሃይማኖት ዶግማ፣ ቀኖናና ትውፊት መሰረት መሆኑን የማረጋገጥ፣ ሥራቸውና ጠባያቸው ከክርስቲያናዊ ሥነ ምግባር ውጭ እንዳይሆን የመከታተልና የመቆጣጠር ኀላፊነት አለበት፡፡ በሰንበት ት/ቤት ያልተመዘገቡ ወጣቶችን እንዲመዘገቡ፣ በሃይማኖትና በሥነ ምግባር እንዲጸኑ ያደርጋል፡፡

6. ሀ) ስጦታዎችን ይቀበላል፤ ለሚመለከተው ክፍልም ያሳውቃል፡፡
ለ) በአጥቢያው ቤተ ክርስቲያን ስም ይከሳል ፤ ይከሰሳል፡፡

7.ከቤተ ክርስቲያኑ ጠቅላላ ገቢ ውስጥ በቃለ ዐዋዲው በአንቀጽ ፶፯ ተራ ቁጥር 1 መሰረት ለኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ጠቅላላ አስተዳደር፣ ለትምህርት፣ ለስብከተ ወንጌል፣ ለልማት፣ ለበጐ አድራጎት እና በየሰበካው ለሚከናወኑት የኅብረት ሥራ ዕቅዶችና ለልዩ ልዩ አገልግሎት የሚያስፈልገውን ገንዘብ ከማንኛውም ገቢ ላይ አቅም እንደፈቀደ እንዲከፈል ያደርጋል፡፡

8.በማእከል ደረጃ ተፈቅዶ አዲስ ሕንጻ ቤተ ክርስቲያ፣ ትምህርት ቤት፣ ክሊኒክና የመሳሰሉት በሚሰሩበት ጊዜም ቢሆን ከግለሰብ፣ ከልዩ ልዩ ድርጅቶችና ከበጎ አድራጊዎች በርዳታ ከሚገኘው በስተቀር ከልማትም ሆነ ከማናቸውም ገቢ ላይ አቅም እነደፈቀደ እንዲከፈል ያደርጋል፡፡

9.የቤተ ክርስቲያኑን ሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤ ጽ/ቤትና የሥራ ክፍሎችን ያቋቁማል፡፡

10.ከባንክ ገንዘብ ወጪ በሚደረግበት ጊዜ፡-
ሀ) መደበኛው የቤተ ክርስቲያኑ ወጪ ሒሳብ በገንዘብ ያዡውና በሰበካው ም/ሰብሳቢ በሁለቱ ጣምራ ይፈረማል ፤ ከመደበኛ ወጪ ሌላ ገንዘብ ማውጣት ሲያስፈልግ በሰበካ ጉባኤ ተወስኖ ለማንኛውም ወጪ በወጪ መጠየቂያ ቅፅ ከተሞላ በኋላ በሥራ ላይ እንዲውል ይሆናል፡፡

ለ) ለሕንጻ ሥራው ወጪ ሲያስፈልግ በኮሚቴው ተወስኖ በአስተዳዳሪና በሕንጻ አሠሪ ኮሚቴ ሰብሰቢ ወይም ሰብሳቢው በሌላ ጊዜ በ ም/ሰብሳቢ ጣምራ ፊርማ በወጪ ማዘዣ ቼክ እየተፈረመ ገንዘቡ እንዲወጣና በሥራ ላይ እንዲውል ያደርጋል፡፡

11.በአጥቢያው ቤተ ክርስቲያን ውስጥ የተቋቋሙት የሥራ ክፍሎች የሚወስኑትን ልዩ ልዩ ጉዳዮች እየመረመረ ያሻሽላል ፣ ይሽራል፣ ያጸድቃል፡፡

12.የአጥቢያው ቤተ ክርስቲያን አገልጋዮች በሚያደርሱት ጥፋት አስተዳደር ነክ የሆነውን አይቶና መርምሮ ውሳኔ ይሰጣል፡፡ ወንጀል ነክ ጉዳዮች በሕግ እንዲታዩ ያደርጋሉ፡፡

13.በዚህ ቃል ዐዋዲ አንቀጽ ፯ ተራ ቍጥር 1 (ለ) መሰረት በየስድስት ወር በሚደረገው ሰብሰባና የሰበካ መንፈሳዊ አስተዳደር ጉባኤ የሥራ ጊዜውን ከመፈጸሙ ከአንድ ወር በፊት ስለአከናወናቸው ሥራዎችና የገንዘብ ወጪዎች በማስመልከት ሪፓርት ለካህናትና ምእመናን ጉባኤ ማቅረብ አለበት፡፡

14. በቤተ ክርስቲያኒቱ በዐበይት በዓላትና በበዓለ ንግሥ ጊዜ በዓሉን ለማሳመር በሚል ከቀኖና ቤተ ክርስቲያን ዉጪ የሚፈጸሙትን ተግባራት እንዳይፈጸሙ ይቈጣጠራል፤ ይከላከላል፡፡

15. በቤተ ክርስቲያኑ ዐውደ ምሕረትና አካባቢው የድምፅ ማጉያዎችን / በካይ ድምፆችን/ በመጠቀም የካሴትና የልዩ ልዩ ሽያጮችንና ፈቃድ ከተሰጣቸው ውጭ የሚካሄድን ልመና እንዳይካሄድ ይቈጣጠራል።

16. በማሕሌት፣ በጸሎተ ቅዳሴ፣ በትምህርተ ወንጌልና መንፈሳዊ አገልግሎት በሚሰጥበት ጊዜ በቅጽረ ቤተ ክርስቲያን በሚገኙ አዳራሾችና ልዩ ልዩ መጠለያዎች ሌሎች መርሐ ግብሮች እንዳይካሄዱ ይቈጣጠራል፣ ይከላከላል፡፡

17. የአጥቢያው ቤተ ክርስትያን ሰበካ መንፈሳዊ አስተዳደር ጉባዔ ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ተጠሪነቱ ለምእመናንና ለሐገር ስብከቱ ጽ/ቤት ይሆናል

# አንቀጽ - 12
## የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ሰበካ መንፈሳዊ ጉባዔ
## ጽ/ቤትና የሥራ ክፍሎች መቋቋም፡-

1.የአጥቢያ ሰበካ መንፈሳዊ አስተዳደር ጉባዔ (ስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ) በዚህ ደንብ አንቀጽ 2 ና 4 የተገለጸውን ዐላማና ተግባር ለመፈጸም እንዲችል አንድ ጽሕፈት ቤትና ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ክፍሎች ያቋቁማል።

ሀ) የስብከተ ወንጌል ክፍል
ለ) የመንፈሳዊ ትምህርት ክፍል
ሐ) የካሕናት አገልግሎት ክፍል
መ) የሰንበት ት/ቤት ክፍል
ሠ) የዕቅድና ልማት ክፍል
ረ) የምግባረ ሠናይ (በጎ አድራጎት) ክፍል
ሰ) የንዋየ ቅድሳት የንብረትና የቅርሳቅርስ ክፍል
ሸ) የሒሳብ ክፍል
ቀ) ገንዘብ ያዥ
በ) የቁጥጥር ክፍል
ተ) የሕንጻ እድሳትና ጥገና ክፍል

2.በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) በተራ ቁጥር (ሀ) እስከ (ተ) የተዘረዘሩት የሥራ ክፍሎች የሥራ ዓይነትና ጠባይ እንደተጠበቀ ሆኖ ተመሳሳይ የሆነውና የማይቃረነውን ክፍል ሁለት ሶስቱን አንድነት በመደራረብ በአንዳንድ የስራ ኀላፊዎች ማሠራት ይቻላል። እንደሁኔታው እየታየ ኮሚቴ ለሚያስፈልጋቸው ክፍሎች ኮሚቴ ማቋቋም ይቻላል።

3.አበል ከሚቆረጥላቸው አገልጋዮች ሌላ በበጎ ፍቃድ እንዲያገለግሉ የሚመረጡት የየክፍሉ ኀላፊዎች የአገልግሎት ዘመናቸው በቃለ ዐዋዲው በአንቀጽ 11 ተራ ቁጥር 2 ስለ ሰበካ መንፈሳዊ አስተዳደር ጉበኤ (ስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ) አባላት የአገልግሎት ዘመን በተመለከተው መሰረት ይፈጸማል፡ ስለሆነም የየክፍሉ የሥራ ኀላፊዎች ምርጫ የሚያደርገው የአጥቢያው ሰበካ መንፈሳዊ አስተዳደር ጉባዔ (የስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ) አባላት ከተመረጡ በኃላ ይሆናል፡

4.በአጥቢያ ቤተክርስቲያን ሥር የተቋቋሙት የሥራ ክፍሎች ተጠሪነታቸው ለቤተ ክርስቲያኑ አስተዳዳሪ ይሆናል።

## አንቀጽ - 13
### የካህናት አገልግሎት ክፍል ሥራና ኀላፊነት

1. ይህ ክፍል የቤተ ክርስቲያንን የውስጥ አገልግሎትና የክህነት ተግባርን የሚያጠቃልል ሆኖ ቄሰ ገበዙን፣ ሊቀ ዲያቆኑን፣ ሊቀ ጠበብቱንና አጋፋሪውን እያስተባበረ ይሠራል።

2. ሥርዓተ ማሕሌቱ፣ ሰዓታቱ እና ቅዳሴውም ሆነ ሌላው መንፈሳዊ አገልግሎት ትክክለኛውን ሥነ ሥርዓት ይዞ እንዲካሄድ ይከታተላል፤ ይቆጣጠራል።

3. ካህናት የንስሐ ልጆቻቸውን ከክሕደት፣ ከኑፋቄ፣ ከክፉ ልማድና ግብር ለመጠበቅ እንዲችሉ ከትምህርት ክፍሉ ጋር በመተባበር በትምርተ ወንጌል እንዲሠለጥኑ ያደርጋል፤ ያስተምራል፤ ይቆጣጠራል።

4. መምህራን፣ ቀሳውስት፣ መዘምራን፣ ዲያቆናትና ሌሎችም የቤተ ክርስቲያን አገልጋዮች በየተግባራቸው ላይ በሰዓቱ ተገኝተው የተመደቡበት የክፍል ሥራቸውንና መንፈሳዊ አገልግሎታቸውን ሳያጓድሉ በስነ ሥርዓት መፈጸማቸውን እየተቆጣጠረ ሁኔታውን ለጽ/ቤቱና ለአስተዳዳሪ በማቅረብ ተገቢውን ይፈጽማል፤ ያስፈጽማል።

5. ልዩ ልዩ መንፈሳዊ አግልግሎት ለምእመናን ሁሉ በእኩልነትና በትክክል እንዲዳረስ ያደርጋል።

6. በቤተ ክርስቲያኑና በጠቅላላው በኢጥቢያው ሰበካ ውስጥ የመንፈሳዊ አግልግሎትን፣ የካህናት ተልእኮንና ተግባርን በሚመለከት ጉዳይ ላይ ስለሚፈጠሩ ሁኔታዎች ጽ/ቤቱንና አስተዳዳሪውን እያሳሰበ አስፈላጊውን ይፈጽማል፤ ያስፈጽማል።

7. መስበክ፣ ማጥመቅ፣ ቀድሶ ማቁረብ፣ ናዝዞ ማሰናበት በአጠቃላይ አማንያን በሃይማኖት እንዲጸኑና በሥነ ምግባር እንዲጎለምሱ ማድረግ የካህናት ተልእኮና ግዴታ መሆኑ እንዲታወቅ ያደርጋል፤ ካህናቱም ለዚህ ሥራ ብቁ እንዲሆኑ ያዘጋጃል።

8. የቃል ትምህርት ያጠና፣ ዳዊት የደገመ እና አምስቱ አዕማደ ምሥጢራትን ያወቀ ግብረ ገብነቱና መንፈሳዊ ዝንባሌው በካህናትና በምእመናን የተመሰከረለትን ለዲቁና ማዕረግ እንዲቀርብ ያደርጋል፡፡

9. መዝገበ ቅዳሴ የተማረ፣ ሰዓታት፣ ኪዳን፣ ሊጦንና መስተብቁዕ አጠናቅቆ ያወቀ፣ ቅኔና ሰባቱ ምሥጢራተ ቤተ ክርስቲያንን ያጠና፣ ቅዱሳት መጻሕፍትን ተርጉሞ ማስተማር የሚችል፣ ግብረ ገብነቱና መንፈሳዊነቱ በሰበካው ቤተ ክርስቲያን ካህናትና ምእመናን የተመሰከረለትን ዲያቆን የቅስና ማዕረግ እንዲቀበል ለቤተ ክርስቲያን አስተዳዳሪ ያቀርባል፡፡

10. የኢትዮጵያ ተዋህዶ ሃይማኖት እምነት ተከታይ ያልሆኑ ነገር ግን እምነቱንና ቀኖናውን ተምረው ክርስቲያን መሆን የሚፈልጉ ሰዎች ጥያቄ ሲያቀርቡ ካህናቱ ሃይማኖቱንና ሥርዓቱን በማስተማር ካሳመኗቸው በኋላ እንዲጠመቁ ይደረጋል፤ ጥያቄው መፈጸሙንም ይቆጣጠራል።

11. የካሕናት አገልግሎት ክፍል መጽሐፍቶችን ልዩ ልዩ ጽሑፎችን የመዝሙር ሲዲዎችን ከኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ሐይማኖት እምነት ውጭ አልመሆናቸውን ካረጋገጠ በኋላ ለሽይጭ እንዲቀርቡ ይፈቅዳል

12. ዐበይት በዓላት በሚከበሩበት ጊዜ ስለ በዓሉ አፈጻጸም መርሐ ግብር አዘጋጅቶ ለሰበካው መንፈሳዊ አስተዳደር ጉባኤ (ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ) ያቀርባል፤ መርሐ ግብሩንም ያስፈጽማል፡፡

13. የቤተ ክርስቲያን አገልጋዮች አግባብነት በሌላቸው ስፍራዎች እንዳይገኙ ይመክራል፤ ይቆጣጠራል፡፡

14. ሥራቸው ያልታወቀና ክህነታቸው ያልተመረመረ ግለሰቦች ቄስ ወይም መነኩሴ በመምሰል ለምእመናን የንስሐ አባት እየሆኑ በቤተ ክርስቲያን አገልግሎት ላይ ችግር እንዳይፈጥሩ ይቆጣጠራል፤ ለምእመናንም ትምህርት ይሰጣል፡፡

15. በስመ ዲያቆን፣ በስመ ቄስና በስመ መነኩሴ ማዕረገ ክህነት ያላቸው ለመሆኑ ያልታወቁ ካህናት በውክልና እንዳይቀድሱ እና የውስጥ አገልግሎት እንዳይፈጽሙ በጥብቅ ይቆጣጠራል፡፡

## አንቀጽ - 14

### የአጥቢያው ሰበካ ቤተ ክርስቲያን አስተዳዳሪ ሥልጣንና ተግባር

በቃለ ዐዋዲው በአንቀጽ 5 እና 6 በዚህ መተዳደሪያ ደንብ አንቀጽ 2 እና 4 ላይ የተመለከተውን ዐላማና ተግባር ለመፈጸምና እና ለማስፈጸም አስተዳዳሪው የሚከተለው ሥልጣንና ተግባር ይኖረዋል፡፡

1. የቤተ ክርስቲያኑ አስተዳዳሪ የሰበካው ቤተ ክርስቲያን ዋና ስራ አስፈጻሚ በመሆን ይህን መተዳደሪያ ደንብ ተከትሎ በሚወጣው የውስጥ ደንብ መሰረት ስለ ሰበካው ካህናትና ምእመናን መንፈሳዊ ጉባኤና ስለ አስተዳደሩ ጉባኤ የሥራ አፈጻጸም በአጥቢያ ሰበካ ቤተ ክርስቲያን ላለው መንፈሳዊ አገልግሎትና አስተዳደር ኀላፊና ተጠሪ ነው፡፡

2. ስለ ቤተ ክርስቲያን አገልጋዮች መንፈሳዊ አገልግሎትና አስተዳደር ከቅዱስ ሲኖዶስ በወጣውና በሚወጣው ደንብ መሰረት የአጥቢያውን ሰበካ ቤተ ክርስቲያን አስተዳደርና መንፈሳዊ አገልግሎት ይመራል፡፡

3. የአጥቢያው ሰበካ ጉባኤ ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ምርጫ ከመከናወኑ በፊት ለአጥቢያው ቤተክርስቲያን ምእመናን የግንዛቤ ትምህርት ይሰጣል፤ እንዲሰጥም ያደርጋል፡፡

4. በአጥቢያው ሰበካ ውስጥ በዚህ መተዳደሪያ ደንብ አንቀጽ 12 ላይ የተዘረዘሩት ንኡሳን ክፍሎች እንዲደራጁና በትክክል ሥራ ላይ እንዲውሉ ተገቢውን ክትትልና ቍጥጥር ያደርጋል፡፡ የልዩ ልዩ ክፍል ሥራ ኀላፊዎችን ያስተባብራል፣ ይቈጣጠራል፡፡

5. የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያኑ አገልጋዮች ካህናትና ምእመናን የአባልነት መታወቂያ ያላቸው መሆናቸውንና በአጥቢያው ሰበካ ውስጥ ያሉት ምእመናን ሁሉ መመዝገባቸውን፤ የጥምቀት፣ የጋብቻ እና የሙታን መዛግብት እየተሠራባቸው መሆኑን ያረጋግጣል፥

6. የአጥቢያውን ሰበካ ምእመናንና የምእመናኑንም ልጆች ከኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ሃይማኖትና ምግባር እንዳይወጡ ያስተምራል፤ ይጠብቃል፤ ያስጠብቃል፤ በጠቅላላው ካህናት ይልቁንም የንስሐ አባቶችን በማስተማሩና በጥበቃው ተግባር እንዲጠናከሩ መመሪያ ይሰጣል፤ ይቈጣጠራል፡፡

7. የቤተ ክርስቲያኑ ገቢ በትክክል እንዲሰበሰብ ገንዘቡና ማንኛውም የሚንቀሳቀስና የማይንቀሳቀስ ሀብትና ንብረት እንዲጠበቅና በአስተዳደሩ ጉባኤ እየታየ በሚወሰነው መሰረት በተገቢው ሥራ ላይ መዋሉን ይከታተላል፡፡

8. ከበላይ በተፈቀደው ዓመታዊ የገንዘብ ድልድል (በጀት) መሰረት ማንኛውንም ወጪ በማዘዝ እንዲሠራበት ያደርጋል፡፡

9. የሰበካው አስተዳደር ጉባኤ እንዲሰበሰብ ጥሪ ያስተልፋል፤ በጉባኤ በተሰጠው ውሳኔ መሰረት እንዲሠራበት እያደረገ አፈጻጸሙን ይቈጣጠራል፡፡

10. የአጥቢያውን ሰበካ መንፈሳዊ አስተዳደር ጉባኤ አባላትን እና የልዩ ልዩ ክፍል ኀላፊዎች ምርጫ ለሐገረ ስብከቱ ጽሕፈት ቤት ያሳውቃል።

11. በአጥቢያ ሰበካ መንፈሳዊ አስተዳደር ጉባኤ ስም አስተዳዳሪው ስለ ሰበካው ካህናትና ምእመናን ሁኔታ፣ ስለ ቤተ ክርስቲያኑ አገልጋዮች፣ ስለ ገንዘብና ንብረት እንዲሁም ስለ ልዩ ልዩ ክፍሎች የሥራ ክንውን መግለጫ ለሰበካው ቤተ ክርስቲያን ካህናትና ምእመናን መንፈሳዊ ጉባኤ በዓመት ሁለት ጊዜ ያቀርባል፤ የጉባኤውንም ውሳኔ ለሐገረ ስብከቱ ጽህፈት ቤት ክህነት ያስተላልፋል፡፡

12. አስተዳዳሪው ቅጥርን፣ ደመወዝ ጭማሪን፣ እድገትና፣ ዝውውርንና ከሥራ ማሰናበትን የሚመለከቱ ጉዳዮችን ሁሉ የሰበካው ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ሳይነጋገርበትና ሳይወስን በተጨማሪም የበላይ አካል ሳያውቀውና ሳይፈቅድ ብቻውን መፈጸም አይችልም፡፡

13. በየዘርፉ ካሉ የሥራ ኀላፊዎች በሚቀርብለት ሪፖርት መሰረት የአገልጋዮችን የሥራ ሂደት ይቈጣጠራል፤ ይመክራል፤ አጥፊዎችንም ይገሥጻል፤ የቃልና የጽሑፍ ማስጠንቀቂያ ይሰጣል፡፡

14. በቃለ ዐዋዲው መሰረት በሚሰጠው መመሪያ የሚወሰንለትን ተግባር ሁሉ ይፈጽማል፤ ያስፈጽማል፡:

15. ለልደት ለጋብቻና ለሌሎች አገልግለቶች በሚስጡ የምስክር ሰንዶች ላይ አግልግሎቱን የፈጸመው ካሕን ስም እንዲጠቀስ ተደርጎ የደብሩ አስተዳዳሪ ይፈርማል:

## አንቀጽ - 15

የአጥቢያው ሰበካ መንፈሳዊ አስተዳደር ጉባኤ
ም/ሰብሳቢ ሥልጣንና ተግባር

1.የቤተ ክርስቲያኑ አስተዳዳሪ በሌለ ጊዜ ም/ሰብሳቢው የአስተዳዳሪውን ተግባር ይፈጽማል (ትፈጽማለች)።
2.ምክትል ሰብሳቢው ከአስተዳዳሪው ጋር በተፈቀደው በጀት ቼክ ላይ በጣምራ ይፈርማል(ትፈርማለች)
3.ም/ሰብሳቢው ሥልጣነ ክህነት የሌለው ከሆነ ምሥጢራተ ቤተ ክርስቲያንን የሚመለከቱ ጉዳዮችን ማየት አይችልም(አትችልም)
4.ም/ሰብሳቢው ተጠሪነቱ(ተጠሪነቷ) ለቤተ ክርስቲያኑ አስተዳዳሪ ነው።
5.የአስተዳደር ጉባዔው ሰብሳቢ ም/ሰብሳቢውን ሲወክለው(ሲወክላት) ሌሎች ተጨማሪ ተግባራትን ያከናውናአል(ታከናውናለች)

## አንቀጽ -16

የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤ
ዋና ጸሓፊ ሥልጣንና ተግባር

1.የአጥቢያው ሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤ ዋና ጸሓፊ ክህነት ያለው ወይንም ምእመን ብቃት ያለው(ያላት)ተጠሪነቱም(ተጠሪነቷም) ለቤተ ክርስቲያኑ አስተዳዳሪ ሆኖ በሰበካው ቤተ ክርስቲያን ጽ/ቤት ውስጥ የሚከናወኑትን ጠቅላላ የጽሕፈት፣ የሒሳብና የንብረት አጠባበቅ ሥራዎችን እንዲዚሁም የልዩ ልዩ ክፍሎችን የሥራ ሂደት በቅርቡ እየተከታተለ(እየተከታተለች) በመቆጣጠር ይሠራል (ትሠራለች) ያሠራል(ታሠራለች)።

2.የአጥቢያው ሰበካ ካህናትና ምእመናን እየተመዘገቡ የአባልነት መታወቂያ ካርድ እንዲያገኙ ያደርጋል(ታደርጋለች)።

3.ሕፃንም ሆነ ዐዋቂ ክርስትና ሲነሳ በመዝገበ ጥምቀት፣ እንዲሁም ጋብቻቸውን በቤተ ክርስቲያን የፈጸሙ ተጋቢዎች በጋብቻ የክብር መዝገብ እንዲመዘገቡና የምስክር ወረቀት እንዲሰጣቸው ያደርጋል(ታደርጋለች)፤

4.መዝገብ ቤቱን ያደራጃል(ታደራጃለች)፣ ሥራውም በሥርዓት እንዲመራና ልዩ ልዩ ጽሑፎች፣ መዛግብት፣ ማኅደረ ጉዳዮች ሁሉ እንዲጠበቁና የጽ/ቤቱ ማኅተም በመዝገብ ቤት ተቀምጦ እንዲሰራበት ያደርጋል(ታደርጋለች)፤ የመዝገብ ቤት ሠራተኛ በሌለበት ጊዜም ደርቦ ይሠራል(ትሠራለች)።

5.የአኃዛዊ መረጃ /የስታትስቲክስ/ ሠራተኛ በሌለበት በሕይወት ያሉትንና በሞት የተለዩትን የምእመናን ስም እየመዘገበ (እየመዘገበች) በክብር እንዲቀመጥ ያደርጋል (ታደርጋለች)።

6.ስለ ቤተ ክርስቲያኑ የሥራ አፈጻጸምና የሒሳብ ይዘት መግለጫ ለመጭው ዓመት ከሚፈቀደው ዓመታዊ የገንዘብ ድልድል (በጀት) ጋር አዘጋጅቶ (አዘጋጅታ) በአስተዳዳሪው አማካይነት ለአስተዳደር ጉባኤው ያቀርባል (ታቀርባለች)።

7.የአጥቢያ ሰበካ መንፈሳዊ አስተዳደር ጉባኤው ጸሐፊ ሆኖ (ሆና) በስብሰባው ላይ በመገኘት ጉባኤው የተነጋገረባቸውን ዝርዝር ጉዳዮችና ውሳኔ የተሰጠበትን ቃለ ጉባኤ ያዘጋጃል (ታዘጋጃለች)፣ አባላቱ እንዲፈርሙበት ያደርጋል (ታደርጋለች)፤ በጸሐፊነቱ (በጽሐፊነቷ) ይፈርማል (ትፈርማለች)።

8.በቤተ ክርስቲያኑ ጠቅላላ ሰበካ ውስጥ ሃይማኖትን፣ የቤተ ክርስቲያንን መንፈሳዊና ማኅበራዊ አገልግሎት በሚመለከት ጉዳይ ላይ ስለሚፈጠሩ ሁኔታዎች አስተዳዳሪውንና የሰበካ መንፈሳዊ አስተዳደር ጉባኤውን እያሳሰበ (እያሳሰበች) እንዲጠና ያደርጋል (ታደርጋለች)።

9.የቤተ ክርስቲያን ካህናትና ልዩ ልዩ ሠራተኞች በየተግባራቸው እየተገኙ መሥራታቸውን በመቈጣጠር ሁኔታውን በየጊዜው ለአስተዳዳሪው በማቅረብ ተገቢውን ይፈጽማል (ትፈጽማለች)፤ ያስፈጽማል (ታስፈጽማለች)።

10.የሰበካውን ቤተ ክርስቲያን አባላትና አገልጋዮች ሁኔታ፣ የገንዘብና ንብረት መግለጫ፣ የጽ/ቤቱንና ከሰበካው ልዩ ልዩ የሥራ ክፍሎች የሚቀርብለትን የሥራ ክንውን እንዲሁም አኃዛዊ መረጃዎችን በማጠቃለል በየሦስት ወሩ ለሰበካ መንፈሳዊ አስተዳደር ጉባኤው ሪፖርት ያቀርባል (ታቀርባለች)።

11.ከአስተዳዳሪውና ከሰበካ መንፈሳዊ አስተዳደር ጉባኤው የሚታዘዘውን ማንኛውንም የቤተ ክርስቲያን ሥራ ይፈጽማል (ትፈጽማለች)፤ ያስፈጽማል (ታስፈጽማለች)።

12.የሰው እጥረት ባለበት ቦታም፣ የሰበካ መንፈሳዊ አስተዳደር ጉባኤው ሲወስን የሒሳብ ሥራና ኀላፊነትን ደርቦ ይሠራል (ትሠራለች)፤

13.ከሰበካ ጉባዔው ሰብሳቢ ጋር በመመካከር መደበኛና አስቸኳይ የአባላት ጠቅላላ ጉባዔን፡ የአስተዳደር ጉባዔንና የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ስብሰባዎችን ቦታ ቀንና ሰዓት ቀደም አድርጎ (አድርጋ) ለሚመለከታቸው ያስውቃል (ታስውቃለች)
14.የቤተክርስቲያኑን የሙዳየ ምጽዋትና ስለት ማከማቻ ሳጥን ቁልፍ ከሚይዙት አንዱ ይሆናል (ትሆናለች)፤ ከፍተኛ ግምት ያላቸው ሰነዶች የሚቀመጡበትን የባንክ ሣጥን (safety Box) ቁልፍ ይይዛል (ትይዛለች)።

## አንቀጽ - 17
### የምክትል ፀሐፊ ተግባርና ሐላፊነት

ምክትል ጸሐፊው (ጸሐፊዋ) ዋና ጸሐፊው (ጸሐፊዋ) በሌለበት (በሌለችበት) ጊዜ ሁሉ የዋና ጸሐፊውን (ጸሐፊዋን) ሥራ ተከቶል ይሠራል (ተከትላ ፤ ትሠራለች) በተጨማሪም የመዝገብ ቤት ክፍሉን ሥራ በሐላፊነት ያከናውናአል (ታከናውናለች) እንዲሁም ከሰበካ ጉባዔው የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል (ታከናውናለች)።

## አንቀጽ - 18
### የገንዘብ ያዥ ተግባርና ኃላፊነት

1.ከምዕመናንና ከተለያዩ የገቢ ምንጮች ለቤተ ክርስትያኑ የሚገባውን ገንዘብ በደብረ ገነት ቅዱስ አማኑኤል ወኪዳነ ምሕረት ሐላፊነት ታትሞ በሚወጣው በአንድ ዓይነት ሕጋዊ ደረሰኝ ብቻ ይሰበስባል (ትሰበስባለች)።
2.ማንኛውንም ለቤተክርስቲያኑ የተሰበሰበ ገንዘብ ከሦስት የሥራ ቀናት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ በቤተ ክርስቲያኑ ስም በተከፈተ የባንክ ሂሳብ ውስጥ አስገብቶ (አስገብታ) ደረሰኙን ይይዛል (ትይዛለች) ፤ ኮፒም ለሂሳብ ሹሙ ያስረክባል (ታስረክባለች)።
3.የቤተ ክርስቲያኑን ገቢና ወጪ ለቁጥጥር በሚያመች ሁኔታ እየመዘገበ (እየመዘገበች) ያስቀምጣል (ታስቀምጣለች)።
4.ገንዘብ ነክ ሰነዶችንና ቼኮችን ይይዛል (ትይዛለች) ፤ የወጪ ማዘዣ በአስተዳደር ጉባኤው ሰብሳቢ ተፈርሞ በሂሳብ ሹሙ ተረጋግጦ ሲደርሰው ወጪ ያደርጋል (ታደርጋለች) ፤ ኃላፊነት ከተሰጣቸው የአስተዳደር ጉባኤ አባላት ጋር በቼክ ላይ ይፈርማል (ትፈርማለች)።
5.የቤተ ክርስቲያኑን የሙዳየ ምጽዋትና ስለት ማከማቻ ሳጥን ቁልፍ ከሚይዙት አንዱ ይሆናል (አንዷ ትሆናለች) ፤ ከፍተኛ ግምት ያላቸው ሰነዶች የሚቀመጡበትን የባንክ ሣጥን (safety Box) ቁልፍ ይይዛል (ትይዛለች)።
6.የበጀት ዓመቱ ከማለቁ ከሁለት ወራት በፊት በባንኩና በሣጥን ያለውን ገንዘብ የየወሩን ገቢ ከባንክ መረጃ ጋር ገምግሞ (ገምግማ) የተከታዩን ዓመት በጀት በመስራት የበጀቱን ዝርዝር ለአጥቢያው ሰበካ መንፈሳዊ አስተዳደር ጉባዔ ጽሕፍት ቤት ያቀርባአል (ታቀርባለች) :
7.ዓመታዊም ሆነ ወርኃዊ ሒሳብ እንዲመረመር ሲታዘዝ የገቢና የወጪ ሰነዶችን በማቅረብ ያስመረምራል (ታስመረምራለች)፥
8.ማንኛውም የገንዘብ ወጭ ከተፈቀደው ና ከተወሰነው $1,500 በላይ መጠባበቂያ እንዳያልፍ ይቆጣጠራል (ትቆጣጠራለች) ይጠብቃል (ትጠብቃለች) :
9.ከአስተዳደር ጉባኤውና ከሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴው የሚሰጡትን ተጨማሪ ተግባራት ያከናውናል (ታከናውናለች)።

## አንቀጽ - 19

### የሂሳብ ሹም ተግባርና ኃላፊነት

1.የቤተክርስቲያኑን ገቢና ወጪ በመደበኛ መዝገብ ላይ እያሰፈረ (እያሰፈረች) በየወሩ ከገንዘብ ያዡ (ያዧ) ጋር በማመሳከር ትክክለኛነቱን ያረጋግጣል (ታረጋግጣለች)፤ ይህኑንም ለቤተክርስቲያኑ የአስተዳደር ጉባኤ ሰብሳቢ በየወሩ ሪፖርት ያደርጋል (ታደርጋለች)።

2.ከአስተዳደር ጉባኤ ሰብሳቢውና ከጸሐፊው ጋር በመሆን በጀት ያዘጋጃል (ታዘጋጃለች) በመንፈሳዊዉ ሰበካ ጉባዔ ሲፈቀድ በትክክል ተግባራዊ መሆኑን ይከታተላል (ትከታተላለች)። በየወሩ መጨረሻ ሒሳቡን በመዝጋት የወሩን ገቢ ወጭውንና ከወጭ ቀሪውን በሰንጠርዥ እያዘጋጀ (እያዘጋጀች) ለጽ/ቤቱ ያቀርባአል (ታቀርባለች)።

3.ማንኛውም የገንዘብ ወጪ ከተፈቀደውና ከተወሰነው በጀት በላይ እንዳያልፍ ይቆጣጠራል (ትቆጣጠራለች)፤ ይጠብቃል (ትጠብቃለች)።

4.በጀት በሚደለደልበት ጊዜ ለሚደለደለው በጀት በቂ ገንዘብ መኖሩን ያረጋግጣል (ታረጋግጣለች)።

5.የበጀት ዓመቱ ከማልቁ ከሁለት ወራት በፊት በባንክና በሣጥን ያለውን ገንዘብ የየወሩን ገቢ ገምግሞ (ገምግማ) የተከታዩን ዓመት በጀት በመሥራት የበጀቱን ዝረዝር ለአጥቢያው ሰበካ መንፈሳዊ አስተዳደር ጉባኤ ጽ/ቤት ያቀርባል (ታቀርባለች)።

6.የሒሳብ ሰነዶችንና ቼኮችን በጥንቃቄ ይይዛአል (ትይዛለች)። የባንኩ ሒሳብ በወቅቱ መታረቁን ያረጋግጣል (ታረጋግጣለች)።

7.የገንዘብ አያያዝ ሥራዎች በትክክል መከናወናቸውን፤ ማናቸውም ወጪ በወጪ ማዘዣ ከተፈቀደውና በአስተዳደር ጉባኤው ወይም በሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴው ውሳኔዎች ከጸደቀው ጣሪያ በላይ አለመሆኑንና ወጪው ከበጀት ጋር የተገናዘበ መሆኑን ይከታተላል (ትከታተላለች)።

8.ተከፋይ እዳዎች በወቅቱ መከፈላቸውን ያረጋግጣል (ታረጋግጣለች)።

9.ከአስተዳደር ጉባኤውና ከሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴው የሚሰጡትን ተጨማሪ ተግባራት ያከናውናል (ታከናውናለች)።

10.የቤተክርስቲያኑን የሙዳየ ምጽዋትና ስለት ማከማቻ ሳጥን ቁልፍ ከሚይዙት አንዱ ይሆናል (አንዷ ትሆናለች)፤ ከፍተኛ ግምት ያላቸው ሰነዶች የሚቀመጡበትን የባንክ ሣጥን (safety Box) ቁልፍ ይይዛል (ትይዛለች)።

## አንቀጽ - 20

### የንብረት፣ የንዋይ ቅድሳትና የቅርሳ ቅርስ ክፍል ሥራና ኀላፊነት

1.ከታቦተ ሕጉ ጀምሮ የቤተ ክርስቲያን ንዋያት ቅድሳት፣ አልባሳት፣ መጻሕፍትና ልዩ ልዩ ንብረቶች ሁሉ ለዚሁ ሥራ ተመርጦ በተመደበ ካህን (ቄስ ገበዝ) በጥንቃቄ እየተመዘገቡ እንዲጠበቁ ያደርጋል፡፡

2.የሰበካ ጉባኤውን አላቂና ቋሚ ዕቃዎችና የሚንቀሳቀሱና የማይንቀሳቀሱ ንብረቶችን በየዓይነታቸው ለይቶ ይመዘግባል፡፡

3.ወጪ ሆነው ለሥራ የሚሰጡትን ዕቃዎችንና ንብረቶች በደረሰኝ ያስረክባል፤ ወጪ የተደረጉ ንብረቶንም ሥራ ላይ መዋላቸውንና መጠበቃቸውን ይቈጣጠራል፤ የሚመለሱትንም መርምሮ ይረከባል፡፡

4.የቤተ ክርስቲያኑን ሕንፃና ቅጥር ግቢ በመቆጣጠር ጥገና የሚያስፈልግ ሲሆን ኃሳብ ለመንፈሳዊዉ ሰበካ ጉባዔው ማቅረብ፡ በጽዳት መጠበቃቸውን ማረጋገጥ ይኖርበታል። በቤተ ክርስትያን ታሪካዊ ቅርሳ ቅርሶች ላይ ጉዳት እንዳይደርስ አስፈላጊውን ጥበቃ ያደርጋአል።

5.በአጥቢያው ቤተ ክርስቲያን ሰበካ መንፈሳዊ ጉባዔ ንብረትና ታሪካዊ ቅርሳ ቅርስ ኀላፊ ሆኖ የሚመደበው ካሕን የገንዘብ ጉድለት ያልተገኘበት በንብረት ማባከንም ሆነ በሌላ ወንጀል ተከሶ በጉባኤ ያልተወሰነበት በፍርድ ቤት ያልተፈረደበት መሆኑን ያረጋግጣል።

## አንቀጽ - 21

### የስብከተ ወንጌል ክፍል ሥራና ኃላፊነት

1.የስብከተ ወንጌል ክፍል የእለቱን የዘወትር መርሐ ግብር በማዘጋጀት በዕለተ ሰንበትና በዓበይት በዓላት ለሕዝበ ክርስቲያኑ ትምህርት እንዲሰጥ ያደርጋአል።

2.አመች በሆነ ጊዜና ቦታ ምእመናንን በመሰብሰብ የቅዱሳት መጻሕፍትን ትምህርት ያስጠናል፡፡

3.በቅዳሴ ጊዜ የዕለቱ ወንጌል ከተነበበ ወይም ከቅዳሴው ፍጻሜ በኋላ ትምህርተ ወንጌል መሰጠቱን ይከታተላል፡፡

4.ምእመናን በሚረዱት እና በሚያውቁት ቋንቋ ትምህርተ ወንጌል እንዲሰጥ፣ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ሃይማኖት ተከታዮች እንዲበዙና በሰበካ ጉባኤው እንዲመዘገቡ በማድረግ ሐዋርያዊ ተልእኮውን ይፈጽማል፤ ያስፈጽማል፡፡

5.በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ጠቅላይ ቤተ ክህነት ጽ/ቤት በስብከተ ወንጌልና ሐዋርያዊ ተልእኮ መመሪያ እየተዘጋጁ የሚወጡትን ጋዜጦች፤ መጽሔቶችና ልዩ ልዩ እትሞችን እየተቀበለ ለምእመናን በወቅቱ የማድረስ ኃላፊነት አለበት፥

6.በሊቃውንት ጉባኤ ታይተውና በማእከል ተፈቅደው የታተሙ መጻሕፍት፣ ጋዜጦች፣ ካሴቶች፣ ሲዲዎች ፣ ዲቪዲዎች ሶሻል ሚድያ እና ልዩ ልዩ እትሞች በቤተ ክርስቲያኑ ዐውደ ምሕረትና በቅጽሩ ዙሪያ ለምእመናን እንዲሰራጩ ያደርጋል፥

7.ከኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ሃይማኖት ውጭ የሆኑ መጻሕፍት፣ ጋዜጦች፣ ካሴቶች፣ ሲዲዎች፣ ቪሲዲዎች፣ ዲቪዲዎች እና ልዩ ልዩ እትሞች ለምእመናን እንዳይሠራጩ ይቆጣጠራል፡፡

8.ያለ ፈቃድ እንሰብካለን እናስተምራለን የሚሉትን ሕገ ወጥ ግለሰቦችን የመቆጣጠር ኃላፊነት አለበት፥

## አንቀጽ - 22

### የመንፈሳዊ ትምህርት ክፍል ሥራና ኃላፊነት

1.እያንዳንዱ የሰበካ ቤተ ክርስቲያን አቅሙ በሚፈቅድለትና ከቅዱስ ሲኖዶስ በሚሰጠው መመሪያ መሠረት በቤተ ክርስቲያን አካባቢ መንፈሳዊ ት/ቤት እንዲቋቋም ያደርጋል፡፡

2.በዚህ ትምህርት ቤት

ሀ) የንባብ፣ የጽሕፈት፣ የሰሌትና የቋንቋ፤

ለ) የጸዋትወ ዜማ፣ የአቋቋምና የቅዳሴ፤

ሐ) የግእዝ (ቅኔ)፤

መ) የትርጓሜ መጻሕፍት (ትምህርተ ሃይማኖት)፤

ሠ) የቤተ ክርስቲያን ታሪክ፤

ረ) የኪነ ጥበባት፣ የተግባረ እድና ልዩ ልዩ የሙያ ትምህርቶች እንዲሰጡ ያደርጋል፡፡

3.የአጥቢያ ሰበካውን ሕፃናት እያሰባሰበ ፊደል ከማስቆጠር ንባብ ከማስተማር ጋር መሠረተ ሃይማኖትን እንዲያውቁና ክርስቲያናዊ ሥነ ምግባር እንዲኖራቸው ማድረግ ተቀዳሚ ተግባሩ ይሆናል፡፡

4.ስለ ትምህርቱም ከቅዱስ ሲኖዶስ በሚወጣው ደንብና ሥርዓተ ትምህርት መሠረት መርሐ ግብር በማዘጋጀት የትምህርቱን ይዘትና አመራር ይከታተላል፡፡

5.ሕፃናት በሥነ ምግባርና በሃይማኖት ተኮትኩተው እንዲያድጉ ያደርጋል፡፡

6.የትምህርት መስጫ ቦታዎች (ጉባኤ ቤቶች) አሠራርና አቀማመጥ ለትምህርት አሰጣጥና ለጤንነት ተስማሚ እንዲሆኑ ያደርጋል፡፡

7.የአጥቢያው ቤተ ክርስቲያን መደበኛ መምህራን ጉባኤያቸውን ሳይፈቱ በየሳምንቱ እሑድ፣ በወርና በዓመት የሚደርሰውን ቃለ እግዚአብሔር ለአገልጋዮች ካህናት ቀደም ብለው እንዲያስጠኑ መርሐ ግብር ያዘጋጃል፡፡

8. ቤተ መጻሕፍት እንዲቋቋምና በሥርዓት እንዲያዝ ካህናቱም በተወሰነ ጊዜ በቤተ መጻሕፍት እየተገኙ በማንበብ ዕውቀታቸውን እንዲያሻሽሉና አእምሮአቸውም በትምህርት እንዲበለጽግ ለማድረግ አስፈላጊውን ሁሉ ይፈጽማል።

9. በማእከል በተዘጋጀ ሥርዓተ ትምህርት መሠረት የተመረጡ መጻሕፍትን ለትምህርት እንዲያገለግሉ የማቅረብ ኀላፊነት አለበት።

10. ተማሪዎች በየዕለቱና በየሰዓቱ በትምህርት ገበታ ላይ እየተገኙ የሚሰጣቸውን ትምህርት መከታተላቸውን ይቆጣጠራል፤ የትምህርት ችሎታቸውንም ይመዘናል።

11. መምህራንም ሆኑ ተማሪዎች ቤተ ክርስቲያንን የማገልገልና የማስገልገል ግዴታ ያለባቸው መሆኑ ያሳውቃል፤ ያስፈጽማል።

12. በእያንዳንዱ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን የሚገኙት መምህራንና ተማሪዎች በሰበካ ጉባኤው ጽ/ቤት ተመዝግበው መታወቂያ እንዲኖራቸውና እያንዳንዱ ተማሪ ትምህርቱን ፈጽሞ በሚወጣበት ጊዜ በመምህሩ፤ በሰበካ መንፈሳዊ አስተዳደር ጉባኤውና በሀገረ ስብከቱ ጽ/ቤት አማካይነት የትምህርት ማስረጃ የምስክር ወረቀት እንዲሰጠው ያደርጋል።

## አንቀጽ - 23
### የሰንበት ት/ቤት ክፍል ሥራና ኃላፊነት

ስለ ሰንበት ት/ቤት ወጣቶች በቅዱስ ሲኖዶስ ፈቃድ የሚወጣውን ደንብና መመሪያ እየተከታተለ የሰበካው የሰንበት ት/ቤት ክፍል ቀጥሎ የተዘረዘሩትን ተግባራት ያከናውናል፡፡

1. የሰንበት ት/ቤትን በአጥቢያው ሰበካ ቤተ ክርስቲያን ያቋቁማል፣ ያደራጃል፣ በአጥቢያው ሰበካ ከአራት ዓመት ጀምሮ የሚገኙት ሕፃናትና ወጣቶች የሰንበት ት/ቤት አባላት ይሆናሉ፡፡ ዲያቆናት በመማርና በማስተማር፣ ቀሳውስትና መምህራን በማስተማር በሰንበት ት/ቤቱ እንዲሳተፉ ያደርጋል፡፡

2. ለሕፃናትና ለወጣቶች እንደየዕድሜያቸው መጠን መምህር በመመደብ በማዕከል ደረጃ በሚወጣው ሥርዓተ ትምህርት መሠረት ትምህርት መሰጠቱን ይከታተላል፡፡

3. በሰንበት ትምህርት ቤት ውስጥ ተምረው የማስተማር ብቃት ያላቸውን እየመረጠ ተጨማሪ ሥልጠና በመስጠት የበላይ አካልን እያስፈቀደ እንዲያስተምሩ ያደርጋል፡፡ ያልተፈቀደላቸው እንዳያስተምሩ ይቆጣጠራል፤ ይከላከላል፡፡

4. በሰንበት፣ በዐበይት በዓላትና ቀናት የዕለቱንና የሳምንቱን መርሐ ግብር በማውጣት የቤተ ክርስቲያን ሕግና ሥርዓት፣ የሃይማኖት ትምህርት፣ የቅዳሴ ተስጥዎና የቅዱሳት መጻሕፍት ጥናት እንዲሰጥ ያደርጋል፡፡

5. ሕፃናትና ወጣቶች በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ሃይማኖት እንዲጸኑ የቤተ ክርስቲያንን ሕግ ሥርዓት እንዲያውቁና እንዲያከብሩ፣ ግብረገብ እንዲሆኑ ከአስተዳደሩ መመሪያ እየተቀበለና በቅርብ እየተከታተለ ያስተምራል፤ ይመክራል፤ ይቆጣጠራል፡፡

6. ለምእመናን ትምህርት የሚሰጡ፣ በሊቃውንት ጉባኤ የተመረመሩና በማዕከል የተፈቀዱ መንፈሳዊ መዝሙራትን እንዲያጠኑ የዕለትና የሳምንት መርሐ ግብር ያዘጋጃል፡፡

7. ከሰንበት ተማሪዎች በበዓላትም ሆነ በሌላ ዝግጅት ጊዜ በትርኢት መልክ በሚቀርበው መንፈሳዊ ዝግጅት በቅድሚያ ለሰበካ መንፈሳዊ አስተዳደር ጉባኤ ጽ/ቤት ቀርቦ ከተመረመረና ከተጠና በኋላ ሲፈቀድ በሥራ ላይ እንዲውል ያደርጋል፤ አፈጻጸሙንም ይከታተላል፡፡

8.የሰንበት ት/ቤት ተማሪዎች በማንኛውም መንገድ ለመንፈሳዊ አገልግሎት የሚሰበሰቡት ገንዘብ ለአጥቢያው ሰበካ ጉባኤ ገንዘብ ቤት ገቢ ይሆናል። ለሚያስፈልጋቸው ወጪ ዝርዝር ጥናቱ ለሰበካው መንፈሳዊ አስተዳደር ጉባኤ ቀርቦ ሲፈቀድ በሥራ ላይ እንዲውል ያደርጋል።

9.ማንኛውንም የሚሰበስቡትን ሀብት ገንዘቡን በቤተ ክርስቲያኒቱ ለአጥቢያው ሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤ ጽ/ቤት ገቢ ያስደርጋል። ገንዘቡንና ንብረቱንም በአጥቢያ ሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤ ያስመረምራል።

10.ቀሳውስት የንስሓ ልጆቻቸው ልጆች መንፈሳዊውን ትምህርት እንዲከታተሉ ወላጆችም ልጆቻቸው በሰንበት ት/ቤት ተመዝግበው መንፈሳዊውን ዕውቀት እንዲቀስሙ ማድረግ ክርስቲያናዊ ግዴታቸው መሆኑን ያሳውቃል፤ ይከታተላል፡

11.የሰንበት ት/ቤት ተማሪዎች መንፈሳዊውን በዓል በሚያከብሩበት ጊዜ የቤተ ክርስቲያናችን እምነትና ሥርዓት በተከተለ ሁኔታ የመለያ ልብስ (ዩኒፎርም) እንዲዘጋጅላቸው ያስደርጋል።

12.በሰበካ ጉባኤ ወይም ከዚያ በላይ በሆነ አካል ካልታወቀና በጽሑፍ ካልተፈቀደ በስተቀር በሰንበት ት/ቤት ስም የአዳር መርሐ ግብር እንዳይደረግ በጥብቅ ይከታተላል፤ ይቆጣጠራል።

13.ከስብከተ ወንጌልና መንፈሳዊ ት/ቤት ክፍሎች ጋር በመተባበር መምህራንን እየጋበዙ ለሰንበት ት/ቤት ተማሪዎች ብቃትና ጥራት ያለው ትምህርት እንዲሰጣቸው ያስደርጋል።

## አንቀጽ - 24

### የዕቅድና ልማት ክፍል ሥራና ኃላፊነት

1. የአጭር፣ የመካከለኛና የረጅም ጊዜ ዕቅድ በማውጣት ልዩ ልዩ የሥራ ዕቅዶች ማስፈጸሚያ ገንዘብ፤ የዕቃ፤ የዕውቀትና የጉልበት ዕርዳታና መዋጮ ከምእመናን፣ ከልዩ ልዩ ድርጅቶች ሊገኝ የሚችልበት ሁኔታ እያጠና ለሰበካው መንፈሳዊ አስተዳደር ጉባኤ ያቀርባል፡፡

2. ለአጥቢያው ቤተ ክርስቲያን የገቢ ምንጭ የሚገኝበትን ተስማሚ የሥራ መስክ ያዘጋጃል፤ ለንዋየ ቅድሳት፣ ለመጻሕፍት፣ ለአልባሳትና ለሌላም የቤተ ክርስቲያን አገልግሎት የሚውል ያዘጋጃል፡

3. በአጥቢያው ቤተ ክርስቲያን የሚገኙት ካህናት፣ ምእመናንና የሰንበት ት/ቤት ወጣቶችም ያላቸውን ዕውቀት፣ የጥሬ ገንዘብ (ሀብት)፣ ልዩ ልዩ ዕቃዎችና የሰውን ጉልበት ጭምር በማስተባበር ለቤተ ክርስቲያኑ ልማት ሥራ እንዲውል ያስደርጋል፡፡

4. ከልማቱ የሚገኘው ገቢ በሰበካ ጉባኤው ካርኒ እየተሰበሰበና በገንዘብ ቤቱ እየተጠቃለለ በቤተ ክርስቲያኑ ስም በተከፈተ የባንክ ሐሳብ ገቢ ይሆናል፡፡

5. የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያኑ ቦታዎች እንዲለሙ እያጠናና እያስጠና ተግባራዊ እንዲሆን ለሰበካ ጉባኤው ያቀርባል፡፡

6. የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያኑ የይዞታ ቦታዎች ከመመሪያ ውጪ የበላይ አካል ሳይፈቅድ ለሦስተኛ ወገን እንዳይሰጡ ይቆጣጠራል፤ ይከታተላል፡፡

7. የሥራውንም ውጤት በሚመለከት በየሦስት ወር ለሰበካ ጉባኤው ሪፖርት ያቀርባል፡፡

## አንቀጽ - 25

### የምግባረ ሠናይ (በጎ አድራጎት) ክፍል ሥራና ኀላፊነት

1. ይህ ክፍል በአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን የሚገኙትን የሰንበቴ የዕድር የልዩ ልዩ ምግባረ ሠናይ ማህበራትን እና በጎ አድራጊ ግለሰቦችን በማስተባበር አሳዳጊ ያጡ ሕፃናትን ጧሪ ቀባሪ የሌላቸውን አረጋዊያንን የታመሙ ምዕመናንና ችግረኞችን ለመርዳት የሚያስችል ክፍል ነው።
2. ለሕፃናትና ለወጣቶች እንደ የዕድሜያቸው መጠን መምህር በመመደብ በማዕከል ደረጃ በሚወጣው ሥርዓተ ትምህርት መሠረት ትምህርት መሰጠቱን ይከታተላል፡፡
3. መንፈሳዊና ሥጋዊ አኗኗራችው የተሻሻለ እንዲሆን ከካሕናቱ መካከል ካሕን ተመርጦ በተወሰነ ሰዓት እንዲያስተምራቸውና እንዲመክራቸው የትምህርት መርሐ ግብር ያዘጋጃል።

## አንቀጽ - 26

### የቁጥጥር ክፍል ሥራና ኀላፊነት

ተጠሪነቱ ለአባላት ጠቅላላ ጉባኤ ሆኖ የሚከተሉትን ተግባራት የሚያከናውን ሶስት አባላት ያሉት የኦዲት ኮሚቴ በጠቅላላ አባላት ጉባኤ ምርጫ ይቋቋማል፤

1. ኮሚቴው ራሱን ችሎ (Independently) የሚሠራ ሲሆን በየ6 ወር አንድ ጊዜ ለቤተክርስቲያኑ አስተዳደር ጉባኤ፤ በዓመት አንዴ ደግሞ ለአባላት አጠቃላይ ጉባኤ የሂሣብ፤ የንብረትና የሥራ እንቅስቃሴ ሪፓርት በጽሁፍ ያቀርባል። እንዲሁም አጠቃላይ ምርጫ በሚደረግበት ጊዜ ከወጪ ቀሪ ያለውን ሂሳብ መግለጫ በፋይልና በኤልክትሮኒክስ መሣሪያዎች ተቀርጸው የሚገኙ ማናቸውም ሰነዶችና በቤተክርስቲያኑ ስም የተመዘገቡ ተንቀሳቃሽና የማይንቀሳቀሱ ንብረቶችን በሙሉ መዝገቦ የሚቀጥሉት ተመራጮች በሰነድ እንዲረከቡ ቅድመ ዝግጅቶች ያደርጋል፤ እንደተጠናቀቀም የርክክቡን ሥነ ስርዓት በኃላፊነት ያስፈጽማል።

2. ገቢና ወጪውን በየወሩ ተቆጣጥሮ ገንዘቡ በባንክ መቀመጡን ያረጋግጣል፡፡

3. ከሰበካ ጉባኤው ንብረት መዝገብ ጋር አስተያይቶ በንብረት ክፍሉ ኀላፊነት የሚገኙትን ቋሚና አላቂ ዕቃዎችን በየመልካቸው ለይቶ በአገልግሎት ያለቁትን፣ በአያያዝ የተበላሹትን፣ የጎደሉትን፣ የተረፉትንና ያልተመዘገቡትን ንብረቶች ሁሉ እያስቆጠረ ዓይነቱንና ብዛቱን በሠንጠረዥ ተዘጋጅቶ መመዝገቡን እያመሳከረ ይቆጣጠራል።

4. በሂሳብ አያያዝ፤ በሪፖርት አቀራረብ፤ በንብረት አጠባበቅና በማናቸውም ደረጃ በቤተክርስቲያኑ የሥራ እንቅስቃሴ ወይም አፈጻጸም ላይ ጉድለት ቢያገኝ ጉድለት ያደረሰውን ሰው መተማመኛ ካስፈረመ በኋላ ለጠቅላላ የአባላት ጉባኤ ውሳኔ በማቅረብ በፌዴራልና በፔንስልቫኒያ ሕጎች መሠረት ተጠያቂነት እንዲኖረው ያደርጋል።

5- በሰበካ ጉባኤ የተመዘገቡት የኢጥቢያው ቤተ ክርስቲያን ካህናትና ምእመናን የከፈሉት ክፍያ በዚህ ደንብ መሰረት መክፈሉንና ማንኛውም የቤተ ክርስቲያኒቱ ልዩ ልዩ ገቢ በትክክል መግባቱን ይቈጣጠራል፡፡

6. በአጥቢያው ቤተ ክርስቲያን ሰበካ ጉባኤ ለአበልና ለሥራ ማስኬጃ ለወርና ለዓመት ከተፈቀደው በጀት በላይ ወጪ እንዳይሆን ይቈጣጠራል፡፡

7. በአጥቢያው ሰበካ ቤተ ክርስቲያን የሥራ ዘርፎች የሚካሄዱት ሥራዎች ሁሉ በወቅቱ መከናወናቸውን እየተቈጣጠረ ሥራው የሚመለከታቸውን ሠራተኞች በማሰባሰብ ወይም በየክፍሉ በመዘዋወር እንደ አስፈላጊነቱ ስለ ሒሳብ አያያዝና የሞዴሎች አጠቃቀም ተገቢውን መመሪያ ይሰጣል፤ ይቈጣጠራል፡

8. በአጥቢያው ቤተ ክርስቲያን የሚገኙት የስእለትና የሙዳየ ምጽዋት ሣጥኖች ምልክትና መለያ ቁጥር እየተሰጣቸው ብዛታቸው እየታወቀ የተቀመጡበትም ቦታ ግልጽና አስተማማኝ መሆኑን ያረጋግጣል፤ በሰበካው አስተዳደር ጽ/ቤት ያልተመዘገቡና ያልታወቁ ሣጥኖችም ሆኑ ሌሎች የገንዘብ መሰብሰቢያዎችን ሁሉ በቅጽረ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ እንዳይኖሩ በጥብቅ
ይቈጣጠራል፡፡

9. የስእለትና የሙዳየ ምጽዋት ሣጥኖች በሥራ ላይ ከመዋላቸው በፊት በሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ በተመረጡ አባላት፣ አስተዳዳሪው፣ ሒሳብ ሹመና ራሱም ተቈጣጣሪው በሚገኙበት የጋራ ፊርማና በደብሩ ማኅተም መታሸጋቸውንና ሲከፈቱም የፈረሙት አባላት ሁሉ መገኘታቸውን ይከታተላል፡፡

10. በዐውደ ምሕረቱም ሆነ በሌላ ቦታ ሙዳየ ምጽዋትና ጥላ በማዞር ስጋጃ በማንጠፍ ወይም በሌላ መንገድ የሚሰበሰበው ማንኛውም ገንዘብና ልዩ ልዩ ስጦታ ሁሉ በአግባቡ እየተመዘገበ በቤተ ክርስቲያኑ ካርኒ (ደረሰኝ) ገቢ መሆኑን ያረጋግጣል፡፡

11. በስእለትና በሌላም ምክንያት ለቤተ ክርስቲያን የሚሰጡት ብር፣ ወርቅና ልዩ ልዩ ንብረቶች ሁሉ ግምታቸው እንዲታወቅ እና በሕጋዊ መንገድ ገቢ እንዲሆኑ አስፈላጊውን ጥረት ያደርጋል፡፡

12.ከንብረት ክፍሉ ጋር በመተባበር የቤተ ክርስቲያኑን ንብረት በየዓመቱ እያስቈጠረና እየመዘገበ የጎደለውንና የጨመረውን አረጋግጦ ለሰበካው መንፈሳዊ አስተዳደር ጉባኤ ጽ/ቤት ሪፖርት ያቀርባል፡

13.ከንብረት ክፍል ወጪ ሆነው ለሚመለከተው ክፍል የሚሰጡትን ንብረቶች በደረሰኝ እንዲሰጡ ያደርጋል፡፡ የተሰጡትም ሥራ ላይ መዋላቸውንና መጠበቃቸውን ይቆጣጠራል፤ የሚመለሱትንም መርምሮ ትክክል መሆናቸውን አረጋግጦ ንብረት ክፍሉ እንዲረከብ ያደርጋል፡፡

14.ኮሚቴውየሒሳብ ሰነዶቹን መርምሮ ለማረጋገጥ ከውጭ ተቀጥረው ከሚሰሩ ባለምያዎች (certified public accountants) ጋር ይተባበራል።

## አንቀጽ - 27

### የሕንጻ ጥገናና ዕድሳት የሥራ ኃላፊነት

1.የኮሚቴው አባላት ከአምስት የማያንሱና ከሰባት የማይበልጡ ምዕመናን እንዲያካትት ሆኖ ማንኛውም ምእመን የዚህ ኮሚቴ አባል መሆን ይችላል ነገር ግን በቤት እደሳ ልምድና ብቃት ያላቸው አባላት እንዲሳተፉ ሰበካ መንፈሳዊ ጉባዔ ያበረታታል።

2.በየዓመቱ የወራቱን ለውጥ በመከተል ለቤተ ክርስቲያኑ የሚያስፈልገውን የማቀዝቀዣና የማሞቂያ መሣሪያዎች እደሳ እንዲደረግ ለሰበካ መንፈሳዊ ጉባዔው ምክር ያቀርባል። ኮሜቴው በአሉት አባሎች መሰራት አለባቸው የሚሉትን እደሳዎች አቅሙ በፈቀደው መንገድ እንዲሰሩ ያደርጋል።

3.የእደሳውና የጥገናው ኮሚቴ የቤተ ክርስቲያኑ ሥራ ከአባላቱ ችሎታ በላይ ሲሆን የውጭ ባለሙያዎችን ወይም ኩባንያዎች ለመንፈሳዊዉ የሰበካ ጉባዔ ሥራ አስኪያጅ ኮሚቴ ይጠቁማል፣ ምክርም ይሰጣል።
4.ቤተ ክርስቲያኑን በማደስ በኩል እቅድ በማውጣት ምዕመናን በጉልበትም በንዋይም እንዲረዱ ያበረታታል።

## አንቀጽ - 28

### የባለአደራ ኮሚቴ

### የሕግ፣ የሰላምና የእርቅ የባለአደራ ኮሚቴ ሥራና ሀላፊነት

1.የባለአደራ ኮሚቴው የቤተ ክርስቲያኗን ሰላምና አንድነት ያስጠብቃል፤ ቤተ ክርስቲያን በምዕምናን ላይ እንዳይቆለፍ ቁጥጥር ያደርጋል። የዚህ ጉዳይ ባለሥልጣንነቱን በሕግ በጠበቃ አጽፎ በፍርድ ቤት ያረጋግጣል ፤ የቤተ ክርስቲያኑ መስራች አባሎች ከመካከላቸው ያስመራጭ ኮሚቴ አቋቁመው አምስት የባለአደራና ቋሚ አባሎች ኮሚቴ ያስመርጥአሉ ፤ ምርጫአው በየ5 አመቱ ይከናወናል። በመግቢያ ላይ እንደተገልጸው የነዚህም መስራች አባላት ሥም ዝርዝር በዚህ መተዳደሪያ ደንብ በመጨረሻ ገጽ ላይ በዝርዝር ሰፍርዋል።

2.ቤተ ክርስቲያኗን በሚመለከት ዓበይት ጉዳዮችን በማንሳት አስፈላጊውን ሀሳብ በጽሑፍ ለሰበካ ጉባዔ ያቀርባሉ ።

3.በቅዱስ ሲኖዶስ የሚወጡ ሕጎች፣ ደንቦችና ድንጋጌዎች በመንበረ ፓትርያርክ አጠቃላይ ሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤ የሚወሰኑ ውሳኔዎችና መመሪያዎች ለሰበካው ጉባኤ ኀላፊዎችና በጠቅላላው ለካህናትና ለምእመናን በቤተ ክርስቲያን ሕግና ሥርዓት መሠረት ሕጋዊ መመሪያና መግለጫ እየሰጠ እንዲያውቁትና እንዲያጠኑት ያደርጋል።

4.በአጥቢያው ሰበካ ውስጥ በካህናትም ሆነ በምእመናን መካከል የሚፈጠር አለመግባባት ቢኖር ወደ ክስ ደረጃ ሳይደርስ እርስ በእርስ በመተራረም በይቅርታና በዕርቅ እንዲወገድ የተቻለውን ሁሉ ያደርጋል።

5.የክሱ አቤቱታ ሕገ ቤተክርስቲያንን የሚመለከት ሆኖ ሲገኝ የከሳሹና የተከሳሹን የሕግ መብት በመጠበቅ የሁለቱንም ወገን ማስረጃዎች በጥንቃቄ ተመልክቶ የመፍትሄ ሃሳብ ያቀርባል። በቃለ ዐዋዲው በአንቀጽ 63 መሰረት "ማንኛውም የቤተ ክርስቲያን አገልጋይ ካህን ወይም ሠራተኛ በቃለ ዐዋዲው በአንቀጽ 60 ተራ ቁጥር 2 የተደነገገውን ተላልፎ ቢገኝ እንደጥፋቱ ሁኔታ በመጀመሪያ ምክርና ተግሣጽ፣ በሁለተኛ ማስጠንቀቂያ ይሰጠዋል፣ በሦስተኛ ጊዜ ቅጣት ይወሰንበታል፣ ቅጣቱም እንደ ጥፋቱ ክብደት ተመዛዝኖ በገንዘብ ወይም በቀኖና፣ ከሥራ በማዛወር፣ ከሥራ በማገድ፣ ከሥራ በማሰናበት ወይም ከአባልነት በመለየት ሊወሰን ይችላል። ሆኖም የመጨረሻው ውሳኔ ማለት ከሥራ የማሰናበቱ ወይም ከአባልነት የመለየቱ ቅጣት ሊጸና የሚችለው ወደመንበረ ጵጵስናው ሀገረ ስብከት ቀርቦ በሊቀ ጳጳሱ ሲጸድቅ ይሆናል።"

## አንቀጽ - 29

### ይህን መተዳደሪያ ደንብ ስለማጽደቅና ስለማሻሻል

1. ይህ ደንብ በአባላት ጠቅላላ ጉባኤ ከጸደቀ በኋላ በወቅቱ በሥራ ላይ በሚገኙት የቤተክርስቲያኑ የሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤ ሥራ አስፈጻሚ አባላት ከተፈረመበት ቀን ጀምሮ የጸና ይሆናል።
2. እንዳስፈላጊነቱ ከታመነበትና በአባላት ደረጃ ውይይት ተደርጎበት እንዲሻሻል የአባላቱን 2/3ኛ ድምጽ ካገኘ ይህ መተዳደሪያ ደንብ በማናቸውም ጊዜ ሊሻሻል ይችላል።
3. ይህ መተዳደሪያ ደንብ መሠረቱ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ቃለ ዓዋዲ እንደመሆኑ መጠን ቤተ ክርስቲያኒቱ ቃለ ዓዋዲውን በምታሻሽልበት ጊዜ ከዚሁ መሻሻል ጋር እንዲጣጣም አስፈላጊ ሲሆን ይህ ደንብ ሊሻሻል ይችላል።ይህ ደንብ እንዲሻሻል የአባላቱን የድጋፍ ድምጽ ለማግኘት በሚጠራ አጠቃላይ የአባላት ስብሰባ ምልዓተ ጉባኤ የሚኖረው ከተመዘገቡና የአባልነት ክፍያቸውን አጠናቀው ከከፈሉ አባላት ከ2/3ኛው በላይ የተገኙ እንደሆነ ብቻ ነው::

የመተዳደሪያ ደንብ አርቃቂ ኮሚቴ አባላት

1) አቶ በለው አስፋ, ሰብሳቢ
2) ሲስተር ፀዳለ እጅጉ
3) አቶ አሻግሬ መንግስቱ
4) ዶ/ር መላኩ ላቀው, ፀሐፊ
5) አቶ ሰለሞን ተካበ

ደ.ገ.ቅ.አማኑኤል ወኪዳነ ምሕረት ቤተ ክርስቲያን እንዲመሰረት ከJanuary 5th, 2019 በፊት አስተዋጽዎ ያደረጉ ምእመናን

ከJanuary 5th, 2019 በፊት በበጎ ፍቃዳቸው በካሕናቱ ላይ የቀድሞው የደ.ገ.ቅ. አማኑኤል ቤተ ክርስቲያን የአስተዳደር ቦርዱ የሚያደረገው በደልና ኢዲሞክራሲያዊ አሰራር ያስመረራቸው ምዕመናን መደራጀት ጀመሩ። አሰራሩ እንዲስተካከል ፔትሽን በማዘጋጀትና በመፈረም ለአስተዳደር ቦርዱ ቢያቀርቡም ተደማጭነት አላገኙም። ከዚያ በሗላ ገንዘብ እያዋጡ ካሕንን መርዳት እንዲሁም ለጠበቃና ለሌላ ወጭ ማዋል ጀመሩ። እነኝህ ምዕመናን ከዚህ በታች ስማቸው የሰፈረው የደ.ገ.ቅ.አማኑኤል ወኪዳነ ምሕረት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን መስራቾች ሆነው ቀርበዋል።

መልአከ ገነት ቄስ ዳኛቸው ደገፋ ፤ ወ/ሮ ምስራቅ ያለው ነጋሽ ፤ ዶ/ር መለኩ ለቀው ፤ ወ/ሮ ሮማን አበራ ፤ አቶ ታፈሰ ወልዴ ፤ ወ/ሮ መንበረ ምህረቱ ፤ አቶ አብነት በየነ ፤ ወ/ሮ ወይነሸት አለሙ ፤ አቶ ብስራት ገብሩ ፤ ወ/ሮ መድህን ገ/ሐዋርያ ፤ አቶ ወንድም ተፈራ ፤ ወ/ሮ ሄርሜላ አባተ ፤ አቶ ፈቃደ እንደሻው ፤ ወ/ሮ የትምወርቅ ተካ ፤ አቶ መክብብ ገላን ፤ ወ/ሮ እቴነሽ ሙሉ ፤ አቶ በለው አስፋ ፤ ወ/ሮ ጎመጁ አቻምየለህ ፤ አቶ ጥላሁን አፈሳ ፤ ወ/ሮ ትዕግሥት ዘገዬ ፤ ዶ/ር ካስ ዳርጌ ፤ ወ/ሮ ሐና ማርያም ተክሌ ፤ አቶ አቢይ ፍስሀ ፤ ወ/ሮ ሳባ ተስፋዬ ፤ ዶ/ር ቅጣው ነጋሽ ፤ ወ/ሮ ደብሪቱ ለማ ፤ ወ/ሮ መነን ጌታሁን ፤ ወ/ሮ ራሄል ታዬ ፤ አቶ አሳምነው ይፍሩ ፤ ወ/ሮ ብርቱካን ዘውዴ ፤ አቶ ውብሸት ገ/አማኑኤል ፤ ወ/ሮ ገነት አበበ አቶ ፀጋዬ አድማሱ ፤ ወ/ሮ አስቴር በለጠ ፤ አቶ ብርሀኔ አክሊሉ ፤ ወ/ሮ ለምለም መብርሀቱ ፤ አቶ ወርቅነህ ገ/ማርያም ፤ ወ/ሮ ፍሬሕዮት ሐበተማርያም ፤ አቶ ሰለሞን ተካበ ፤ ወ/ሮ ሰብለ ወንጌል መሠረት ፤ አቶ አሻግሪ የሺጥላ ወ/ሮ አዲስዓለም ሐይሉ ፤ አቶ አልዓዛር ወጋየሁ ፤ ወ/ሮ ፌቨን ካሳሁን ፤ ዶ/ር ብርሀኑ አለማየሁ ፤ ወ/ሮ አየለች ሙሉጌታ ፤ አቶ ዳርሲኔ አስፌር ፤ ወ/ሮ ጥሩዓለም ልየው ፤ አቶ ሰለሞን ግሩም ፤ ወ/ሮ ራሄል ታደሰ ፤ አቶ ተፈራ ከበደ ፤ ወ/ሮ ፀሐይ ጌታሁን ፤ አቶ እስክንድር ሩጋ ፤ ወ/ሮ መስከረም ከድር ፤ አቶ ኤፍሬም ካባ ፤ ወ/ሮ ሰራዊት ሰመረ ፤ አቶ ወርቁ አካለ ፤ ወ/ሮ ዘርፌ ፤ አቶ ብስራት ንጉሴ ፤ ወ/ሮ ሃና ገሠሠ ፤አቶ ተድላ ወልዱ ፤ ወ/ሮ ቅድስት አያሌው አቶ ሥዩም ናደው ፤ ወ/ሮ ፀዳለ እጅጉ ፤ አቶ አበበ ተረፈ ፤ ወ/ሮ አበባ ሀይሉ ፤ አቶ ሳሙኤል አድማሱ ፤ ወ/ሮ ዙሪያሽወርቅ ዘለለው ፤ አቶ መስፍን ተገኑ ፤ ወ/ሮ ኒና ምንአለ ፤ ወ/ሮ የሺ ዳዲ ፤ ወ/ሮ ዓይንአለም ከበደ ፤ ወ/ሮ አለምፀሐይ ከበደ ፤ አቶ በለጠ ነጮ ፤ ወ/ር ቅድስት ፀሐይ ፤ ወ/ሮ የውብዳር ተፈራ ፤ አቶ መስፍን ገ/እግዚአብሔር ፤ አቶ ሐረገወይን መሰለ ፤ ወ/ሮ ዲቦራ እምላሰሉ ፤ ወ/ት አስቴር በቀለ ፤ ወ/ሮ እናኑ ታፈሰ ፤ ወ/ሮ እቴነሽ መንገሻ ፤ አቶ ነጋ መኮንን ፤ ወ/ሮ አማነሽ መኮንን ፤ ዶ/ር ብርሀን ተክሌ ፤ ወ/ሮ ሰላማዊት በላቸው ፤ አቶ ስለሺ ሀይሉ ፤ ወ/ሮ ተናኜ ሀይሌ ፤ ወ/ሮ ምሕረት ቶላ ፤ አቶ ዘነበ ገለቱ ፤ አቶ ገዛሀኝ ፀጋዬ ፤ ወ/ሮ ዘብነት ገርሱ ፤ አቶ ቦጋለ ፍስሀ ፤ ወ/ሮ ዮዲት አምሀ ፤ አቶ ሀይሉ አደፍርስ ፤ ወ/ሮ ቃል ኪዳን ፤ አቶ ጥጋቡ ከበደ ፤ ወ/ሮ ይብራአለም ፤ አቶ በላይ በየነ ፤ ወ/ሮ ገነት ደምሴ ፤ አቶ ናቲ ቅጣው ፤ አቶ የሻነህ ተስማ ፤ አቶ ታምራት ይህድጎ ፤ ወ/ሮ ሠርክአለም አዛነው ፤ አቶ ጥላሁን ደገፋ ፤ ወ/ሮ ወይንሸት ሺፈራው።